# የሐጅና ዑምራ አድራጊዎች

በነፃ የሚታደል

## እንዲሁም

# የረሱል ﷺ መስጂድ ጎብኚዎች

# መመሪያ

ቅንብር

ለሑጃጆች ኢስላማዊ ግንዛቤ አስጨባጭ ተቋም

ትርጉም

ጣሀ አህመድ

**የሳዑዲ ዓረቢያ የኢስላማዊ ጉዳዮች**
**የአውቃፍ የዳዕዋና ኢርሻድ ሚኒስቴር**
**የኢስላማዊ ጥናቶች እና ፈትዋ ቋሚ ኮሚቴ**
**እና**
**የሸይኽ ሙሀመድ ኢብኑ ሷሊህ አል-ዑሰይሚን** አላህ ይዘንላቸው
**ድሑፎችን መሰረት ያደረገ**

IBNU MAS'OUD
ISLAMIC CENTER
Spreading pure islamic knowledge

مركز ابن مسعود الإسلامي

‹‹አላህ መልካም የሻለትን ሰዉ ዲኑን ያስገነዝበዋል››
(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል)

የሳዑዲ ዓረቢያ  የኢስላማዊ ጉዳዮች የአውቃፍ የዳዕዋና ኢርሻድ

ሚኒስቴር

# የሐጅና ዑምራ አድራጊዎች

*እንዲሁም*

*የረሱል ﷺ መስጂድ ጎብኚዎች*

# *መመሪያ*

*ቅንብር*

*ለሑጃጆች ኢስላማዊ ግንዛቤ አስጨባጭ ተቋም*

*የኢስላማዊ ጥናቶች እና ፈትዋ ቋሚኮሚቴ*

*እና*

*የሸይኽ ሙሀመድ ኢብኑ ሷሊህ አል-ዑሰይሚን*

*(አላህ ይዘንላቸው)*

*ጽሑፎችን  መሰረት  ያደረገ*

*ትርጉም*

**ጣሀ አህመድ**

# ማውጫ

መግቢያ ........................................................ 3

መቅድም ...................................................... 6

አስፈላጊ ምክሮች ........................................... 8

ኢስላምን የሚያበላሹ ነገሮች ............................ 12

የሐጅን እና የዑምራን ስነ-ስርዓት እንዴት ትፈፅማለህ? እንዴትስ የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጂድ ትጎበኛለህ? 18

የዑምራ አፈፃፀም ስርዓት ................................ 20

የሐጅ አፈፃፀም ስርዓት .................................. 25

በሙህሪም ላይ ግዴታ የሚሆኑ ነገሮች ................... 31

የመልዕክተኛው (ﷺ) መስጅድ ጉብኝት አፈፃፀም ........ 33

አንዳንድ ሑጃጆች የሚፈፅሟቸው ስህተቶች............. 37

ወሳኝና አጫጭር ማሳሰቢያዎች ለሐጅ እና ዑምራ አድራጊዎች እንዲሁም የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጂድ ጎብኚዎች ......................................................... 47

በዓረፋ፣ በመሽዐረል ሀራም እና በሌሎችም ቦታዎች ሊደረጉ የሚችሉ ዱዐዎች......................................... 57

በሱና መርከብ እንሳፈር…………………………….75

# መግቢያ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ አላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላም በመልእክተኛው ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

ሐጅ ከአምስቱ የኢስላም መዕዘናት አንዱ ነው። ግዴታነቱም በቁርአን፣ በሀዲስ እና በዑለማዎች ስምምነት (ኢጅማዕ) የተረጋገጠ ሲሆን አንድ ሙስሊም ጤናማ አዕምሮ ካለው፣ ለአካለ መጠን ከደረሰ፣ ባሪያ ካልሆነ፣ አካላዊ እና ቁሳዊ አቅሙ ከተሟላለት ሐጅ ማድረግ በርሱ ላይ ግዴታ ይሆናል። ታዲያ ይህን ታላቅ ኢስላማዊ ግዴታ ለመወጣት ውድ ገንዘቡን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን መስዋት የሚያደርገ ማነኛውም ሙስሊም ሁለት ቁም ነገሮችን ጠንቅቆ ሊያወቅ ይገዋባል። እነርሱም፦

አንደኛ፦ ስራን ሁሉ ፍፁም ለአላህ ማድረግ (ኢኽላስ) ሲሆን ይህም በአንድ ሰው አምልኮ ውስጥ አንኮር ነጥብ ነው፤ ምክንያቱም ስራው ይህን ካጣ በዱንያ ላይ ድካም ከመሆኑም ባሻገር በአኼራ አይቀጡ ቅጣትን ያስከትላልና። አላህ (ﷻ) በሀዲሰል ቁድሲይ እንዲህ ብሏል፦

«እኔ ከአጋሪዎች ማጋራት እጅጉን የተብቃቃሁ ነኝ። አንድን ስራ በውስጡ ከእኔ ጋር ሌላን አጋርቶበት የሰራ ሰው እሱንም ማጋራቱንም ትቻቸዋለሁ»(ሙስሊም ዘግበውታል)

ሁለተኛ፦ የአላህ መልእክተኛ (ﷺ) በፈፀሙት መልክና ሁኔታ አምልኮን መፈፀም ነው፡፡ ማነኛውም ዒባዳ መልእክተኛው (ﷺ) ከፈፀሙበት ሁኔታ እና ከትእዛዛቸው ውጭ ከሆነ አላህ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም፡፡ ስለሆነም የአላህ መልእክተኛ (ﷺ) እያንዳንዱን የአምልኮ ዘርፍ በንግግር ተናግረው በተግባር ሰርተው አስተመርዋል፡፡ በተለይም ሐጅን በተመለከተ «የሐጅና ዑምራ ስርአታችሁን ከኔ ተማሩ፡፡ »(አህመድ ዘግበውታል) በማለት አሳስበዋል፡፡ እነዚህን ቁም ነገሮች ጠንቅቆ መረዳቱም ይሁን ወደ ተግባር መለወጡ እውቀትን የሚጠይቅ መሆኑ ከማነኛወም ሙስሊም የማይሰውር ሀቅ ነው፡፡

የሐጅን ስነ-ስረዓት ሰንመለከተው በአብዛኛው ተግባር ላይ የተመረኮዘ ከመሆኑ አንፃር ከሌሎቹ የዒባዳ አይነቶች በተለየ መልኩ እውቀትን የሚጠይቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ማህበረሰባችን ስለ ሐጅና አፈፃፀሙ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተውሰነ ደረጃ ለውጥ እያሳየ ቢሆንም ነገር ግን ይበቃዋል የሚባልበት ደርጃ ላይ አልደርሰምና አጋዥ ያስፈልገዋል፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደ ሸኽ ሙህመድ ኢብኑ ሷሊህ አል-ዑስይሚን እንዲሁም በሳዑዲ ዓረቢያ የኢስላማዊ ጥናቶች እና ፈትዋ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ያሉ ታላላቅ ዑላማዎችን ጽሁፎች መሰረት ያደረገውን ይህንን በይዘቱ አነስተኛ፣ ቅደም ተከተሉ ያማረ፣ ቀላል ያገላለጽ ሰልትን የተከተለ፣ ከውስብስብነት የራቀ እና ላያያዝ አመቺ መጽሐፍ ወደ አማርኛ ቋንቋ በመመለስ የግሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሞክሪያልሁ፡፡ ምንም እንኳ ኢስላም ከአንድ ምንጭ የተቀዳ ከመሆኑ አንፃር የመጽሐፉ ጽንሰ ሃሳብ በተመሳሳይ ርዕስ በአገርኛው ቋንቋ ከተፃፉ ሌሎች መጻሀፍት ጋር ቢያመሳስለውም ነገር ግን በውስጡ አስፈላጊ ምክሮች፣ የሐጅ እና ዑምራ አፈፃፀም፣ በስርዓቱ ላይ አንዳንድ ሑጃጆች

የሚፈፅሟቸው ስህተቶች… እና ሌሎችም አንገብጋቢ ጉዳዮች በተወሰነ ደረጃ የተብራሩበት እና የተወሱበት መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉን በመተርጎም ሂደት በተቻለ አቅም የቃል በቃል የትርጉም ስልትን ለመከተል የሞከርኩ ሲሆን ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች የቃል በቃሉ የትርጉም ስልት የማያስኬድ ሆኖ ሲገኝ የነፃ ትርጉም ስልትን ለመከተል ተገድጃልሁ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አጠር ያሉ ማብራሪያዎችን መስጠትም አስፈላጊ ስለነበረ የግርጌ ማስታወሻዎቹን ጨምሪያልሁ። የመጽሐፉ ርዕስ በዓረበኛው "ደሊሉ አልሐጂ ወልሙዕተሚሪ ወዛኢሪ መስጂዲ አረሱሊ" 31ኛው እና እንደ ሂጅሪያ አቆጣጠር የ1430ው እትም ነው። የሰው ልጅ ከመሆኔ አንጻር የትርጉም ስራው ጉድለት አይጠፋውምና በጹሁፉ ላይ ያሎትን አስተያየት abdmuha@gmail.com ወይም በፖ.ሳ.ቁ. 50151 እንደትጽፉልኝ እጠይቃለሁ።

በመጨረሻም ከማንም በላይ አላህን አመሰግናለሁ በመቀጠልም ይህ መጸሐፍ በአጭር ጊዜ ለንባብ እንዲበቃ፣ በኮምፒዩተር በመጻፍ፣ በማረም፣ አስተያየት በመስጠት እና በማሳተም ለተባበሩት ለኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር የስራ ሀላፊዎች እና የዳዕዋ ክፍሉ ላቅ ያለ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

የአላህ ሰላት እና ሰላም በመልእክተኛው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እና ፈለጋቸውን በተከተሉ ላይ ሁሉ ይሁን።

ጣሀ አህመድ

ዙልቃዒዳ 1431 ዓ.ሂ

# መቅድም

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላት እና ሰላም ከርሳቸው በኋላ ነብይ በማይመጣው ነብያችን ሙሐመድ ኢብኒ ዓብደላህ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

ለሑጃጆች ኢስላማዊ ግንዛቤ አስጨባጭ ተቋም ይህንን የሐጅ እና ዑምራ ሕግጋት አፈፃፀም ያቀፈ አነስተኛ መመሪያ መፅሐፍ በማቅረቡ ደስታ ይሰማዋል።ጽሑፉንምበቅድሚያ እራሳችንን በመቀጠልም እናንተን አደራ በምንልባቸው አሳሳቢ ጉዳዮች የጀምረነው ሲሆን ይህምአላህ (ﷻ) በቅርቢቱም ይሁን

በወዲያኛው አለምለስኬት የሚበቁና ትርፋማ የሚሆኑ ባሮቹን በገለፀበት ወቅት የተናገረውን ንግግር መሰረት በማድረግ ነው፤ አላህ (ﷻ) እንዲህ ይላል፦

قَالَ تَعَالَى: ﴿ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلْحَقِّ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلصَّبْرِ ﴿٣﴾ ﴾ العصر: ٣

**ትርጉሙም**፡-«...በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት።»{አል-ዐስር :2-3}

قَالَ تَعَالَى: ﴿ وَتَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلْبِرِّ وَٱلتَّقْوَىٰ ۖ وَلَا تَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ ﴾ المائدة: ٢

**ትርጉሙም**፡-«… በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኀጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡…» {አል-ማኢዳህ ፡2}

አንተ ሐጅ ለማድረግ የተነሳህ ሆይ! የሐጅ ግዴታህን በእውቀት ላይ በተመሰረተ መልኩ እንድትወጣ ወደ ሐጅ ስራ ከመግባትህ በፊት ይህንን መጠነኛ መጽሐፍ ለማንበብ ጥረት እንደምታደርግ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በአላህ ፍቃድም ብዙ ከመጠየቅ የሚያብቃቃህንእውቀት ከውስጡ ትገበያለህ፡፡

የሁሉንም ሐጅ ተቀባይነት ያለው (መብሩር)፣ ድካሙ የተመሰገነ (ሰዕይ መሽኩር)፣ ስራውንም በጎ እና ተቀባይነት ያለው እንዲያደርግ አላህን እንለምናለን፡፡

ወሰላሙ ዓለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱህ

# ለሐጃጆች ምክሮች

እናንተ ሐጃጆች ሆይ! አላህ (ﷻ)ሐጅ ለማድረግ ስላደላችሁ እናመሰግነዋለን፡፡ከሁላችንም በጎ ስራችንን እንዲቀበል ምንዳችንንም እጥፍ ድርብ እንዲያደርግልን እንለምነዋለን፡፡

እነዚህን ምክሮች ለእናንተስንለግስ የሁላችንንም ሐጅ ተቀባይነት ያለው (መብሩር)፣ድካማችንን እና ስራችንን የተመሰገነ (መሽኩር)እንዲያደርግልንበአላህ ላይ ተስፋ ከማድረግ ጋር ነው፡፡

1. የአላህን ብቸኛ አምላክነት (ተውሂድ)፣ለእርሱ ፍጹምመሆንን(ኢኽላስ)፣ለጥሪው ምላሽ መስጠትን፣ እርሱን መታዘዝን፣ ምንዳን ከርሱ መከጀልን እና መልዕክተኛው ሙሐመድን (ﷺ) መታዘዝን መሰረት ባደረገ የተባረከ ጉዞ ላይ መሆናችሁን አስታውሱ፤ ከወንጀል የራቀና ተቀባይነት ያለው ሐጅ(አልሐጅል-መብሩር) ምንዳው ጀነት ነውና፡፡

2. ሸይጣን በመካከላችሁ ጥላቻን እና ጭቅጭቅን እንዳያጭር ተጠንቀቁ፤ እርሱ (ውድቀታችሁን የሚናፍቅ) አድፋጭ ጠላታችሁ ነውና፡፡ ስለዚህ ለአላህ ብላችሁ ተዋደዱ እንዲሁም ክርክርን እና ወንጀልን ራቁ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ማለታቸውን እወቁ፦

(لاَيُؤْمِنُ أَحَدُكُمْ حَتَّى يُحِبَّ لأَخِيهِ مَايُحِبُّ لِنَفْسِهِ)

**ትርጉሙም፦** «አንዳችሁ ለራሱ የወደደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ እምነቱ አልተሟላም፡፡» (ቡኻሪ እና ሙ ስሊም ዘግበውታል)

3. በአጠቃላይ የሀይማኖታችሁም ይሁን የሐጃችሁ ጉዳይ በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ግር የሚላችሁን ጉዳይ የእውቀት ባለቤቶችን(አሊሞችን) ጠይቁ፤ አላህ (ﷻ)

እንዲህብሏልና፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ فَسْـَٔلُوٓا۟ أَهْلَ ٱلذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ﴿٤٣﴾ ﴾ النحل: ٤٣

**ትርጉሙም፡-** «...የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ::» {አል-ነህል :43}

የአላህ መልእክተኛም እንዲህ ብለዋል፡-

من يرد الله به خيرا يفقهه في الدين

**ትርጉሙም፡-** «አላህ መልካም የሻለትን ሰው እምነቱን (ዲኑን) እንዲገነዘብ ያደርገዋል»(ቡኻሪ እና ሙስሊም የዘገቡት)

4. አላህ (ﷻ) ግዴታዎችን (ፈርዶችን) እንደጻፈብን እና በበጎ

ፍቃደኝነት የምንፈጽማቸውን(ሱናዋችን)እንደደነገገልን ሁሉ ግዴታዎቹን (በሰንካላ ምክንያቶች) ካልተወጡ ሰዎች ሱናዎችን እንደማይቀበል እወቁ፡፡ አንዳንድ ሑጃጆች ይህንን እውነታ ባለመገንዘብ ለምሳሌ ሐጀረል-አስወድን[1]

[1] **ሐጀረል አስወድ፡-** ማለት ወደ ካዕባው በር ለዞረ ሰው በስተግራ የሚገኘው ማዕዘን ላይ የሚገኝ ድንጋይ ነው፡፡ ይህን ድንጋይ መሳም ወይም መንካት አልያም በርሱ ትይዩ ሲሆኑ በእጅ ምልክት ማሳየት የመልእክተኛውን (ﷺ) አራያነት መከተል ሲሆን ከዚያ ውጭ ይህ ድንጋይ የማይጠቅም የማይጎዳ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ለዚህም ነው የመልእክተኛው ባልደረባ ዑመር (ረ.ዓ) እንዲህ ነበር ያሉት « ነብዩ (ﷺ)

ለመሳም በጠዋፍ ላይ ረምል[1] ለማድረግ፣ ከመቃመ ኢብራሂም[2] ኋላ ለመስገድ ወይም የዘምዘምን ውሀ ለመጠጣት እና መሰል ሱናዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሉ በከፍተኛ ሁኔታ ምዕመናንወንዶችንና ሴቶችን በመግፋትና በማጨናነቅ ሲያስቸግሩ ይስተዋላሉ፡፡ ምዕመናን ማስቸገር የተከለከለ ነው፡፡ ታዲያ እንዴት ሱናን ለመተግበር ስንል ክልክልን እንፈፅማለን? ስለዚህ እናንተ ሁጃጆች ሆይ! አላህ ይዘንላችሁ ከፊላችሁከፊላችሁን ከማስቸገር ይቆጠብ፡፡ አላህ መልካም ምንዳችሁን ይፅፍላችኋል እጥፍ ድርብም ያደርግላችኋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፦

*ሀ.*በመስጂደል-ሀራምም ይሁን በሌላ ቦታ በማነኛውም ሁኔታአንድ ሙስሊም ወንድ ከሴቶችጎንም ይሁን ኋላ አለመስገድ እስከቻለ ድረስ ሊሰግድ አይገባውም፡፡በአንጻሩም ሴቶች ከወንዶች ኋላ ሊሰግዱ ይገባል፡፡

*ለ.*በሀረም መተላለፊያ መንገዶችም ይሁን በሮች ላይ ሰላትን መስገድ አይገባም፤ ምክንያቱም ይህ ራሳችንናየሚተላለፉ ሰዎችን ማስቸገር ነውና፡፡

---

ሲስሙህ ባላይ ኖሮ አልሰማህም ነበር የማትጠቅም የማትጎዳ ድንጋይ ነህ፡፡»

[1] **ረመል፡-** ማለት እርምጃን ከማቅረብ ጋር መፍጠን ሲሆን ሐጅና ዑምራን አጣምረው ለሚፈጽሙ በመግቢያ ጠዋፍ (ጠዋፈል ቁዱም) ላይ እንዲሁም ዑምራን ለሚያደርጉ ከጠዋፋቸው የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዙሮች ላይ በቻ የሚፈጽሙት ተግባር ነው።

[2] **መቃመ ኢብራሂም፡-** ማለት ነብዩላህ ኢብራሂም (ዓ.ሰ) ከልጃቸው ኢስማዒል ጋር በመሆን ካዕባን በገነቡበት ወቅት ለመቆሚያ የተጠቀሙበት እና የእግራቸው ፋና ያረፈበት ድንጋይ ነው።

*ሐ.*በሰዎች ላይ ጉዳትን እንዲሁም ችግርን የሚያስከትል ከመሆኑ አንፃር መጨናነቅ በሚኖርበት ወቅት በካዕባ ዙሪያ በመቀመጥ በአቅራቢያው በመስገድ ሒጅር[1] ወይም መቃመ ኢብራሂም ጋር በመቆም ጠዋፍ የሚያደርጉ ሰዎችን ማስተጓጎል አይፈቀድም፡፡

*መ.*ሐጀረል-አስወድን መሳም ሱና ሲሆን የአንድን ሙስሊም ግለሰብ ክብር መጠበቅ ደግሞ ግዴታ (ፈርድ) ነው፡፡ስለዚህ ሱናን ተግባራዊ ለማድረግ ስትል ግዴታህን ሳትወጣ እንዳትቀር በሰዎች መካከል መጨናነቅ በሚከሰትብት ወቅት ወደ እሱ እጅህን አንስተህ ማመላከትህ እንዲሁም “አላሁ አክበር” ማለትህ ይበቃሀል፡፡ ከጠዋፍ በምትወጣበት ጊዜርህራሄናእርጋታበተላበሰ መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡

*ሠ.*ጠዋፍ ላይ ላለ ሰው በሩክነል-የማኒ[2] ትይዩ ሲሆን ሱናው “ቢስሚላህ አላሁ አክበር” ከማለት ጋር እርሱን በቀኝ እጁ መንካቱ ቢሆንም መሳሙ ግን አልተደነገገም፡፡ ለመንካት ሳይችል ቢቀርም እጁን በማንሳት ምልክት ሳያሳይ እንዲሁም ‹‹አላሁ አክበር›› ሳይል ጠዋፉን ይቀጥላል፡፡ ምክንያቱም (በዚህ አይነቱ ሁኔታ ላይ)ይህን አይነቱን ድርጊት መፈጸምን በተመለከተ ከመልዕክተኛው (ﷺ) በትክክለኛ ሰነድ የተዘገበ ምንም አይነት አስተምህሮ የሌለ በመሆኑ ነው፡፡ ጠዋፍ ላይ በሩክነል-የማኒ እና በሐጀረል-አስወድ መካከል በሚሆንበትም ወቅት

---

[1] **ሒጅር፦** ማለት ከመልዕክተኛው (صلى الله عليه وسلم) መላክ ጥቂት አመታት በፊት ካዕባ በጎርፍ ተጠቅቶ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ዓረቦች በተለይም ቁረይሾች መልሶ ለመገንባት ተገደው ነበር፤ ሆኖም ቤቱን የሚገነቡበት ከተፈቀዱ (ከሀላል) የገቢ ምንጮች የተገኘው ገንዘብ በማለቁ በአንድ በኩል የቀድሞ መሰረቱን ለማሳውቅ በሚያስችል መልኩ የግማሽ ክብ ቅርጽ ይዞ በጅምር የቀረው ግንባታ ነው።

[2] **ሩክነል የማኒ፦** ማለት ፊቱን ወደ ካዕባ አዞሮ ለቆመ ሰው ሐጀረል አስወድ ካለበት ማዕዘን በስተግራ የሚታየው ማዕዘን ነው።

رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

"ረበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበ-ንናር" ማለቱ ይወደድለታል፡፡

**ትርጉሙም**፡-«...ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን...»{አል-በቀራ፡201}

- በመጨረሻም ዘወትር ቁርዓንና ሀዲስን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ሁሉንም አደራ እንላለን፡፡አላህ (ﷻ) እንዲህ ይላል፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ١٣٢ ﴾ آل عمران: ١٣٢

**ትርጉሙም**፡- «ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ፡፡»{አሊ-ዒምራን ፡132}

# ኢስላምን የሚያበላሹ ነገሮች

- አንተ ሙስሊም ወንድም ሆይ! እጅግ በጣም ብዙኢስላምን የሚያበላሹ ነገሮች እንዳሉ ልታውቅ ይገባሀል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚከሰቱት አስር ያህሉ ሲሆኑ ልትጠነቀቃቸው ይገባል፡፡ እነርሱም፡-

***አንደኛ፡-*** በአምልኮ ላይ ከአላህ ጋር ሌላን ማጋራት፡፡ አላህ ﷻ እንዲህ ይላል፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢﴾ المائدة: ٧٢

**ትርጉሙም**፡-«…እነሆ!በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን(ጀነትን) በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖሪያውም እሳት ናት፡፡ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡» {አል-ማኢዳ ፡72}

*እዚህ አይነቱ ማጋራት ውስጥ ከሚካተቱ ነገሮች መካከል ሙታንን መለመን፣ከጭንቅ አውጡኝ (ድረሱልኝ)ማለት፣ ለእነርሱ መሳል እና ማረድ ናቸው፡፡*

***ሁለተኛ፦*** *አንድ ሰው በእርሱና በአላህ መካከል (ከፍጡራን)የሚማፀናቸውን፣ አማልዱኝ የሚላቸውን እና የሚመካባቸውን አማካይ ካደረገ በዑለማዎች ሙሉ ስምምነት (ኢጅማዕ) መሰረት ከኢስላም ይወጣል፡፡*

***ሶስተኛ፦*** *ከአላህ ውጪ ሌላን የሚያመልኩ ወገኖች (ሙሽሪኮች) ከሀዲያን (ካፊሮች) መሆናቸውን ያላመነ ወይም የተጠራጠረ አልያም አካሄዳቸው ትክክል ነው ያለ ሰው ከኢስላም ወጥቷል፡፡*

***አራተኛ፦*** *ከነብዩ (ﷺ) መመሪያ ውጪ ሌላን መመሪያ ይበልጥ የተሟላ መሆኑንወይም ከእርሳቸው ፍርድ ይልቅ የሌሎች ፍርድ የተሻለ እንደሆነ ያመነ ሰው ከሀዲ ነው፡፡ እዚህ ውስጥከሚካተቱ ሌሎች ነጥቦች መካከል፦*

*ሀ. የተለያዩ ሰዎች የደነገጓቸው ሕግጋት እና የቀረጿቸው ስርዓቶች ከ ኢስላማዊው የሸሪዓ ድርጋጌዎች እና ስርዓቶችየተሻሉ ናቸው ብሎ ማመን፣*

* ወይም ኢስላማዊው ስርዓት (ከተለያዩ ነገሮች አንፃር) በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ብሎ ማመን፣

* ወይም ለሙስሊሞች ኋላቀርነት ምክንያቱ ኢስላም ነው ብሎ ማመን፣

* አልያም ኢስላም በግለሰብ እና በጌታው መካከል ባለ ግንኙነት ላይ የተገደበስለሆነ ሌሎች የሕይወት መስኮችን የሚመለከት አይደለም ብሎ ማመን፡፡

**ለ.**(እጅን ሊያስቆርጥ በሚችል ስርቆት ላይ የተገኘን ሰው) እጅን እንደ መቁረጥ ወይም ከጋብቻ በኋላ ዝሙት ላይ የወደቀን ሰው በድንጋይ መውገር ያሉ ኢስላማዊ የቅጣት ህግጋትን (ሊፈፅሙ በሚችሉባቸው አገራት)ተግባራዊ ማድረግ ካለንበት ዘመን ጋር የሚሄድ አይደለም ብሎ መናገር፡፡

**ሐ.** ሸሪዓዊ በሆኑ ማህበራዊ ግንኙነቶች(ሙዓመላት) ወይም የቅጣት ህግጋት አልያም ከዚያ ውጭ በሆኑ ጉዳዮች አላህ ካወረደው ሕግ ውጭ በሌላ መፍረድ ይቻላል ብሎ ማመን፡፡ ምንም እንኳ ግለሰቡ እነዚያን (አላህ ካወረደው ውጭ ያሉ ሕግጋት) ከሸሪዓዊው ፍርድ ይሻላሉ ባይልም (ይህ እምነቱ) ክህደት ውስጥ ይከተዋል፡፡ ምክንያቱም በሁሉም ዑለማዎች ስምምነት (ኢጅማዕ) መሰረት ግለሰቡ ይህንን በማመኑ አላህ እርም ያደረጋቸውን ይፈቀዳሉ እንዳለ ነውና የሚቆጠረው፡፡ አላህ እርም ያደረጋቸውን እንደ ዝሙት፣አስካሪ ነገሮችን መውሰድ፣ ወለድን መጠቃቀም እና ከሸሪዓ ውጭ ባለመፍረድ ያሉበኢስላም እርምነታቸው ግልፅ የሆኑ

ጉዳዮች ይፈቀዳሉ ብሎ ያመነ በአጠቃለይ የሙስሊሞች ስምምነት (ኢጅማዕ)መሰረት ካፊር ነው፡፡

*አምስተኛ፦*መልዕክተኛው (ﷺ) ከአላህ ይዘው ካመጡት መልዕክት ቅንጣት ታክል አንኳ ብትሆን ከድንጋጌነቱ አንፃር የጠላ ሰው ቢሰራበትም ከኢስላም ይወጣል፡፡ ይህ የአላህ ቃል እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَرِهُوا مَا أَنزَلَ اللَّهُ فَأَحْبَطَ أَعْمَالَهُمْ ۝٩﴾ محمد: ٩

**ትርጉሙም፦** «ይህ እነርሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው፡፡ ስለዚህ *ሥራዎቻቸውን* አበላሸባቸው፡፡» {ሙሀመድ :9}

*ስድስተኛ፦*በአላህ ወይም በመፀሀፉ፣ በመልዕክተኛው (ﷺ) አልያም ከአላህ ዲን መገለጫዎች በአንዱየተሳለቀ (ያላገጠ) በእርግጥ ከኢስላም ወጥቷል፡፡ ይህም አላህ (ﷻ) እንዲህ ስላለ ነው፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿قُلْ أَبِاللَّهِ وَآيَاتِهِ وَرَسُولِهِ كُنتُمْ تَسْتَهْزِئُونَ ۝٦٥ لَا تَعْتَذِرُوا قَدْ كَفَرْتُم بَعْدَ إِيمَانِكُمْ﴾ التوبة: ٦٥ – ٦٦

**ትርጉሙም፦** «…በአላህና በአንቀጾቹ፣ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን?» በላቸው፡፡ አታመካኙ፣ ካመናችሁም በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ፡፡…» {አተውባህ :65-66}

*ሰባተኛ፦*ድግምት መስራት ወይም ማሰራት ከዚሁ የሚካተተው "ሰርፍ" በመባል የሚታወቀው እና አንድ

ግለሰብ ለሚስቱ ያለውን ፍቅር አስረስቶ እንዲጠላት ማድረግን መሰረት ያደረገ ተግባር ነው፡፡ በአንፃሩም "አል-ዐጥፍ" (መስተፋቅር) በመባል የሚታወቀው እና ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ አንድን ሰው የማይወደውን እና የማይፈልገውን ነገር እንዲወደውና እና እንዲፈለገው የማድረግ ተግባር እዚሁ ውስጥ የሚጠቃለል ይሆናል፡፡ በዚህ አይነቱ ስራ የተሰማራ አልያም ድርጊቱን የወደደው ሰው በእርግጥ ከኢስላም ወጥቷል፡፡ ይህም ቀጣዩን የአላህ ንግግር መሠረት ያደረገ ነው፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّىٰ يَقُولَا إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ فَلَا تَكْفُرْ﴾ البقرة: ١٠٢

**ትርጉሙም:-** «…«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም፡፡ …» {አል-በቀራ፡102} ማለት ነው፡፡

***ስምንተኛ፡-*** በሙስሊሞች ላይ (የበላይነትን እንዲያገኙ)አጋሪዎችን (ከሀዲያንን) መርዳትና መተባበር፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ ይላል፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَن يَتَوَلَّهُم مِّنكُمْ فَإِنَّهُۥ مِنْهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ۝٥١﴾ المائدة: ٥١

**ትርጉሙም:-** «…ከናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፡፡ አላህ (ከሀዲያንን ረዳት እና ወዳጅ አድርገው የሚይዙ) አመጸኞችን ህዝቦች አያቀናም፡፡» {አል-ማኢዳ ፡51}

***ዘጠነኛ፦*** አንዳንድ ሰዎች ከመልዕክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) ሸሪዓ ስርዓት ውጪ መሆን ይፈቀድላቸዋል ብሎ ያመነ ሰው ካፊር ነው፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ ብሏልና፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٨٥﴾ ﴾ آل عمران: ٨٥

**ትርጉሙም:-** «ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡» {አሊ-ዒምራን :85}ማለት ነው፡፡

***አስረኛ፦*** ኢስላምን አልያም እርሱን በማወቅ እና ተግባራዊ በማድረግ እንጂ ኢስላም ሊረጋገጥ የማይችልባቸውን አንኳር ጉዳዮች ላለመማር እንዲሁም ገቢራዊ ላለማድረግ መሸሽ ከኢስላም ያስወጣል፡፡ ይህም አላህ (ﷻ) እንዲህ ያለ በመሆኑ ነው፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِۦ ثُمَّ أَعْرَضَ عَنْهَآ ۚ إِنَّا مِنَ ٱلْمُجْرِمِينَ مُنتَقِمُونَ ﴿٢٢﴾ ﴾ السجدة: ٢٢

**ትርጉሙም:-** «በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋተ (ችላ ካለ) ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን፡፡»{አሰጅዳህ :22}

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ عَمَّآ أُنذِرُوا۟ مُعْرِضُونَ ﴿٣﴾ ﴾ الأحقاف: ٣

**ትርጉሙም፡-** «…እነዚያ የካዱትም ከተስፈራሩት ነገር(ችላ ብለው)ዘዋሪዎች ናቸው፡፡»{አል-አሕቃፍ ፡3}

- እነዚህን ኢስላምን የሚያፈርሱ ነገሮች በተመለከተ ተገዶ ከሚፈፅማቸው ሰው ውጭ በቀልድ መልኩ፣ ሆን ብሎ እና(አደጋ ሊደርስብኝ ይችላል በሚል ተጨባጭ ያልሆነ) ስጋትበሚፈፅማቸው መካከል ልዩነት የለም፡፡

- የአላህን አሳማሚ ቅጣት እና ቁጣ ከሚያስከትሉ ነገሮች ሁሉ በእርሱ እንጠበቃለን፡፡

# የሐጅን እና የዑምራን ስነ-ስርዓት እንዴት ትፈፅማለህ? እንዴትስ የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጂድ ትጎበኛለህ?

አንተ የተከበርክ ሙስሊም ሆይ! የሐጅ እና ዑምራ አፈፃፀም ሶስት ዓይነት ስነ-ስርአቶችያሉት ሲሆን እነርሱም፡- አተመቱዕ ፣ አል-ቂራን እና አል-ኢፍራድበመባል ይታወቃሉ፡፡

* ***አተመቱዕ፡-*** ማለት በሐጅ ወራት (ማለትም ከሸዋል ወር መጀመሪያ አንስቶ እስከ የዙልሂጃ ወር አስረኛ ቀን ጎህ መቅደድ ድረስ ባሉት ጊዜያት) ለዑምራ ኒያ (ኢሕራም)[1]

[1] **ኢሕራም፡-** ማለት ሐጅ ወይም ዑምራ ስነ-ስርአት ውስጥ መግባትን መነየት ነው፡፡ አብዛኛው ማህበረሰብ ግን ኢሕራም በማለት የሚጠራው ለወንዶች በኢህራም የተነሳ ከሚከለከሉ ነገሮች መካከል አንዱ በሰውነት አካላት ልክ የተሰፉ ልብሶች ከመሆናቸው ጋር በማያያዝ ወንዶች ከታች ለማሽረጥ ከላይ ለማጣፋት የሚጠቀሟቸውን ሁለት ብትን ጨርቆች ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በማድረግ ዑምራን ጨርሶ (ወደ መደበኛ አኗኗር ከተመለሰ በኋላ) በዚያው አመት ዙልሂጃ 8 ቀን (የወመ-አተርዊያ) ከመካ ወይም ከአቅራቢያዋ ለሐጅ ኒያ (ኢሕራም) ማድረግ ነው፡፡

* ***አል-ቂራን፡-*** ማለት በሐጅ ወራት ዑምራንና ሐጅን በማጣመር በአንድ ላይ በመነየት (ኢሕራም) ማድረግ ሲሆን (በዚህ የሐጅ እና የዑምራ ስርዓት ወደ ሐጅ ለገቡ ሰዎች) እስከ የእርዱ ዕለት (ዙልሂጃ 10) በኢሕራም ላይ መቆየት የግድ ይሆናል፡፡ አልያም (ቂራን ማለት) በሐጅ ወራት ዑምራን ኒያ (ኢሕራም) አድርጎ ከገቡ በኋላ (የዑምራውን) ጠዋፍ[1] ከመጀመር በፊት (በተለያዩ ምክንያቶች) የሐጅ ኒያን በዑምራ ላይ ማካተት ነው፡፡

* ***አል-ኢፍራድ፡-*** ማለት በሐጅ ወራት ከሚቃት[2] ወይም መኖሪያው ከሚቃቱ ክልሎች ውስጥ ለሆነ ሰው ከመኖሪያው፣ አልያም (በተለያዩ ምክንያቶች) በመካ ተቀማጭ የሆነ ከመካ ለሐጅ ብቻ ኒያ (ኢሕራም) ማድረግ

---

[1] **ጠዋፍ፡** ማለት በብቸኝነት ወደ አላህ መቃረብን በማሰብ እንዲሁም የነብያትን አርአያነት በመከተል አላህን በማውሳት ወይም እርሱን በመማፀን አልያም ቁርአንን በማንበብ ከሐጀረል አስወድ ጀምሮ ካዕባን በስተግራ አደርጎ በርሱ ዙርያ ሰባት ግዜ መዞር ነው፡፡

[2] **ሚቃት፡** ማለት በጉዞው ሐጅን ወይም ዑምራን ለሚያስብ ሰው በሐጅና ዑምራ ስርአቶች ውስጥ መግባቱን ሳይነይት ሊያልፈው የማይገባ ክልል ነው፡፡ እነዚህ ክልሎች (ሚቃቶች) አምስት ሲሆኑ አነርሱም፡ ዙል ሑለይፋ፣ አል-ጁሕፋ፣ ቀርነል መናዚል፣ የለምለም እና ዛቱ ዒርቅ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሀገራችንን ጨምሮ በዚህ አቅጣጫ ለሚያልፉ ሐጅና ዑምራ አድራጊዎች የለምለም ሲደርሱ ወይም በርሱ ትይዩ ሲሆኑ ኒያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ነው፡፡ ግለሰቡ ሀድዩ[1] አብሮት ያለ ከሆነ እስከ (ዙልሂጃ 10) የእርዱ እለት በኢህራሙ ላይ ሲቆይ ሀድይ አብሮት ከሌለ ግን ነብዩ (ﷺ) ሀድይ አብሮቸው ሳይኖር ሐጅን ኒያ (ኢሕራም) አድርገው የመጡትን ሰሐቦችባዘዟቸው መሰረት ጠዋፍን፣ ሰዕይን እና ፀጉርን ማሳጠርን በመፈፀም ሐጁን ወደ ዑምራ በመቀየር ሙተመቴዕ እንዲሆን ተደንግጎለታል፡ ፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ቂራንን ነይቶ የነበረሰው ሀድይን ይዞ ካልመጣ ቂራኑን ወደ ዑምራ መቀየር ተደንግጎለታል፡፡

ሀድይን ይዞ ላልተንቀሳቀሰ ሰው ከሶስቱ የሐጅ እና የዑምራ አፈፃፀም ስርዓቶች ተመቱዕ በላጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ነብዩ (ﷺ) በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ይህንን እንዲፈፅሙ ባልደረቦቻቸውን አፅንኦት ሰጥተው አዘዋልና፡፡

# የዑምራ አፈፃፀም ስርዓት

1. ወደ ሚቃት በምትደርስበት ጊዜ እራስህን ማፅዳት፣ መታጠብ እና ከኢሕራም ልብስህ ውጪ አካልህን ሽቶ መቀባት ሱና ይሆንልሀል፡፡ በመቀጠልም የኢሕራም ልብስህን ሽርጥና ኩታህን (ሽርጥህን በማሸረጥ ኩታህን በማጣፋት) ልበስ፡፡(የኢሕራም ልብሶችህን በተመለከተ)የተሻለ የሚሆነው ሁለቱም ነጭ መሆናቸው ነው፡፡ ሴት ልጅን በተመለከተ እስካልተገላለጠች፣ ከወንዶች እና ከካፊሮች ጋር በአለባበስ እስካልተመሳሰለች የፈለገችውን ልብስ ትለብሳለች፡፡ ከዚህ በኋላ ለዑምራ

[1] ሀድይ፦ ማለት ወደ አላህ ለምቃረብ ከበግ ወይም ፍየል አልያም ግመል እና በሬ መካከል በሐረም ክልል የሚሰዋ እንስሳ ነው፡፡

لبيك عمرة

لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ لَبَّيْكَ لَبَّيْكَ لاَشَرِيكَلَكَ لَبَّيْكَ إِنَّ الْحَمْدَ وَالنِّعْمَةَ لَكَ وَالْمُلْكَ لاَشَرِيكَ لَكَ

***“ለበይከ ዑምረተን”***

***“ለበይክ አላሁመ ለበይክ ለበይከ ላ ሽሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢነልሀምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላ ሽሪከ ለክ”*** በማለት ኒያ (ኢሕራም) ታደርጋለህ፡፡

**ትርጉሙም፡-** «አቤት አላህ ሆይ!አሁንም አቤት የዑምራን ስርአት ለመፈፀም(ተዘጋጅቻልሁ)፡፡ አቤት አላህ ሆይ! አሁንም አቤት ለአንተ አጋር የለህም፡፡ ምስጋና፣ፀጋና ንግስናም ለአንተ ነው፡፡ አጋር የለህም፡፡» (ቡኻሪ እና ሙስሊም የዘገቡት)

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን (ተልቢያን)[1] በማለት ላይ ወንዶች ድምፃቸውን ከፍ ሲያደርጉ ሴቶች ግን ድምፃቸውን ከፍ አያደርጉም፡፡ ኒያን ካደረግክበት ሰዓት አንስቶም ተልቢያውን ሌሎች ዚክሮችን እና አላህን ምህረት መጠየቅን (እስቲግፋርን) ታበዛለህ፡፡

2. መካ በምትደርስበትም ወቅት ከሀጀረል-አስወድ ጀምረህ “አላሁ አክበር” በማለት በካዕባ ዙሪያ ሰባት ዙር ጠዋፍ

---

[1] **ተልቢያ፡-** የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም አቤት እሺ ማለትን የሚያመለክት ሲሆን በእዚህ አገባብ የተፈለገው ለአላህ ትእዛዛት እና ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀትን የሚያመለክተው «ለበይክ አላሁም ለበይክ…» የሚለው ቃል ነው፡፡

አድርግ፡፡ በዚህም ወቅት አላህን ማውሳት እንዲሁም ከተደነገጉ የዚክር እና የዱዓእ አይነቶች በፈለግከው እርሱን መለመን ትችላለህ፡፡ በሩክነል የማኒ እና በሀጀረል-አስወድ መካከል ስትሆን የሚከተለውን ማለትህ (ዱዓእ ማድረግህ) ሱንና ነው፡፡

رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

**“ረበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበ-ንናር”**

**ትርጉሙም፡-** «ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን» {አል-በቀራ፡201}

ከዚህ በኋላ ከተመቸ እርቀት ላይ ብትሆን እንኳ ከመቃመ-ኢብራሂም ኋላ፣ካልሆነም በመስጂዱውስጥ በማንኛውም ስፍራ (ሁለት ረከዓ) ትሰግዳለህ፡፡

በዚህኛው ጠዋፍ ለወንድ ልጅ ኢድጢባዕ (ማለትም የኩታውን መሀል በቀኝ እጁ ብብት ስር፤ ጫፎቹን ደግሞ በማጣፋት ግራ ትከሻው ላይ ማድረግ) እንዲሁም በጠዋፉ የመጀመሪያ ሦስት ዙሮች ላይ ብቻ ረምል (እርምጃን ከማቀራረብ ጋር መፍጠን) ሱንና ነው፡፡

3. በመቀጠልም ወደ ሰፋ ኮረብታ በመሄድ (ወደርሱ ስትቀርብ) ይህንን የአላህ ቃል አንብብ፦

قَالَ تَعَالَى: ﴿إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلْمَرْوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِ فَمَنْ حَجَّ ٱلْبَيْتَ أَوِ ٱعْتَمَرَ فَلَا جُنَاحَ عَلَيْهِ أَن يَطَّوَّفَ بِهِمَا وَمَن تَطَوَّعَ خَيْرًا فَإِنَّ ٱللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ ﴿١٥٨﴾﴾

البقرة: ١٥٨

**ትርጉሙም፡-** «ሶፋና መርዋ ከአላህ(ትዕዛዝ መፈጸሚያ) ምልክቶች ናቸው፡፡ ቤቱን (ካዕባን) በሐጅ ወይም በዑምራህ ሥራ የጎበኘ (ያቀደ) ሰው በሁለቱ (መካከል) በመመላለሱ በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም፡፡ መልካምንም ሥራ በፈቃደኛነት የሠራ ሰው (አላህ ይመነዳዋል)፤ አላህ አመስጋኝ(የባሮቹንም ስራ)ዐዋቂ ነውና፡፡» {አል-በቀራ፡158}

በላዩም ላይ ወጥተህ ወደ ካዕባ አቅጣጫ በመዞር ሶስት ጊዜ "አልህምዱሊላህ አላሁ አክበር" በማለት አላህን ከማመስገን ጋር አልቀው፣ ዱዓዕም የሚያደርግ ሰው እጁን እንደሚያነሳው እጅህን ከፍ አድርገህ ሶስት ጊዜ

"لاَإِلَهَ إلاَّاللَّهُ وَحْدَهُ لاَشَرِيكَ لَهُ لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَعَلَى كَلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ أَنْجَزَ وَعْدَهُ وَنَصَرَ عَبْدَهُ وَهَزَمَ الأَحْزَابَ وَحْدَهُ"

**"ላ ኢላሀ ኢለኗህ ወህደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙሉኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ አላኩሉ ሸይኢ ቀዲር""ላ ኢላሀ ኢለኗህ ወህደሁ አንጀዘ ወዕደሁ ወነሰረ ዐብደሁ ወሀዘመል አህዛበ ወህደሁ" በል፡፡**

**ትርጉሙም፦** « ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚግባው አምላክ የለም፡፡ አንድ ነው አጋርም የለውም፡፡ ንግስና ለእርሱ የተገባ ነው፡፡ ምስጋናም ለእርሱ የተገባ ነው፡፡ እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚገባው አምላክ

የለም፡፡ ቃልኪዳኑን ሞልቷል፡፡ ባሪያውንረድቷል። የተሰበሰበውንም የጠላት ጦር ለብቻው አንኮታኩቷል፡፡» [ሙስሊም የዘገቡት]

ይህን ከማለትህም ጋር በየመሃሉ አላህን መማፀንህ ዱዐእህንም ሶስት ሶስት ግዜ ደጋግመህ ማድረግህ ሱንና ነው፡፡ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ዚክሮች የተወሰኑትን ብቻ ብትልም ችግር የለውም፡፡

* ከዚያም ከሰፋ በመውረድ የዑምራህን ሰዕይ[1] ሰባት ግዜ በሰፋና መርዋ መካከል አድርግ፡፡ በሁለቱ አረንጓዴ ምልክቶች መካከል ስትሆን የቻልከውን ያክል ትፈጥናለህ(ትሮጣለህ)፡፡ ከምልክቶቹ በፊት በተለመደው እርምጃህ ትራመድ እንደነበረው ሁሉከምልክቶቹም በኋላ በተለመደው እርምጃህ(ሰዕይህን)ቀጥለህ መርዋ ላይ ትወጣለህ፤ አላህን ታመሰግናለህ ልክ ሰፋ ላይ የፈፀምከውን ድርጊት ትፈፅማለህ፡፡

* ለጠዋፍ እና ሰዕይ የተለየ እንዲሁም ግዴታ የሆነ ዚክር የሌለ ሲሆን ይልቁኑ ጠዋፉን እና ሰዕዩን የሚፈጽመው ግለሰብ ከነብዩ (ﷺ) በትክክለኛ ሰነድ ለተዘገቡት ዚክሮች እና ዱዓዎች ትኩረት ከመስጠት ጋር ከዚክር እና ዱዓዕ አልያም ቁርዓንን ከማንበብ የገራለትን ይፈፅማል፡፡

4. ሰዕይህን በተሟላ መልኩ ከጨረስክፀጉርህን ተላጨው ወይም አሳጥረው ሆኖም ሙተመተዕ ከሆንክ መላጨትህን

---

[1] **ሰዕይ፦** ማለት በሰፋና መርዋ ኮረብታዎች መካከል ወደ አላህ ለመቃረብ እርሱን እያወሱ፣ እየተማፀኑና እያመሰገኑ የሚከናወን የሰባት ግዜ ምልልስ ነው፡፡

ከሐጅ ተህሉል[1] ለምታደርግበት ወቅት አቆይተኸው ለአሁኑ ፀጉርህን ማሳጠርህ በላጭ ነው፡፡ በዚህ ተግባርህ ዑምራህ የተሟላ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ (ሙተመቲዕ ከሆንክ ነው ) በኢሕራም የተነሳ የተከለከልካቸው ነገሮች (መሕዙራቱል-ኢሕራም) ሁሉ ይፈቀዱልሃል፡፡

* በተጨማሪም ሙተመተዕ ወይም ቃሪን ከሆንክ አንድ በግ (ፍየል) በግልህአልያም ከግመል እና በሬ አንዱን ለሰባት በእርዱ ዕለት (ከዚያም በኋላ ባሉ ሶስት ተከታታይ ቀናት) ማረድ ግዴታ ሲሆንብህ ይህንን ማድረግ ካልቻልክ አስር ቀን (ሶስቱን በሐጅ ላይ ሰባቱን ወደ ቤተሰቦችህ ስትመለስ) መፆም ግዴታ ይሆንብሀል፡፡

* እዚህ ላይ ሶስቱ (የፆም) ቀናት ከዓረፋ ዕለት(ዙልሒጃ 9) በፊት ያሉት ቀናት ቢሆኑ የተሻለሲሆን ነገር ግን ከዒድ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት(አያሙ አተሽሪቅ) ብትጾምም ችግር የለውም፡፡

# የሐጅ አፈፃፀም ስርዓት

1. “ሙፍሪድ” ከሆንክ (ሐጅን ብቻ ከሆነ የምታደርገው) ወይም ሐጅና ዑምራን በማጣመር የምትፈፅም “ቃሪን”ከሆንክ አንተ በምታልፍበት መንገድ ካለው “ሚቃት” (ኢሕራም የማድረጊያ ቦታ) ኢሕራም (ኒያ) አድርግ፡፡

[1] ተህሉል፡- የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም መፈታት የሚል ሲሆን በዚህ አገባብ የሚፈለገው በኢሕራም የተነስ ተከልክለው የነበሩ ነገሮች መፈቀዳቸውን ነው፡፡

- ኢሕራም ከማድረጊያው ስፍራ “ሚቃት” (ወደ መካ) አልፎ በሚገኝ ስፍራ ያለህ እንደሆነ ከአለህበት ቦታ ከሶስቱ የሐጅ እና ዑምራ አፈፃፀም ስርኣቶች አንተ በፈለግከው ኢሕራም አድርግ፡፡

- “ሙተመቲዕ”(በሐጅ ወራት ዑምራን አድርጎ ካጠናቀቀ በኋላ ሐጅን የሚያደርግ) ከሆንክ ለዑምራ አንተ የምታልፍበት መንገድ ላይ ካለው ሚቃት ለሐጅ ደግሞ ዙልሒጃ ስምንት ቀን (የውመ አተርዊያ) ካለህበት ቦታ ኢሕራም (ኒያ) አድርግ፡፡ ሁኔታዎች ከተመቻቹልህ ታጠብ፣ሽቶም (ሰውነትህን ብቻ) ተቀባ ቀጥሎም የኢሕራም ልብሱን (ሽርጥና ኩታውን) ልበስ፡፡ ከዚያም “ለበይከ ሐጀን፤ለበይከ አላሁመ ለበይክ፤ለበይከ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ፤ ኢነልሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ” በል፡፡

2. በመቀጠልም ወደ ሚና በመሄድ የዙህር፣የዐስር፣ የመግሪብ፣የኢሻዕ እና የፈጅር ሰላቶችን በወቅታቸው (ጀምዕ ሳታደርግ) ባለ አራት ረከዓ የሆኑትን ሁለት ሁለት ረከዓ (ቀስር) በማድረግ ስገድ፡፡

3. ከዙልሒጃ የዘጠነኛው ቀን ፀሐይ ከወጣች በኋላ በእርጋታ ወደ ዓረፋ ተጓዝ፡፡ (በተለይም) በዚህ ወቅት ሐጅ ለማድረግ የመጡወንድሞችህን ከማስቸገር ተጠንቀቅ፡፡ በዚያው በዓረፋ ምድር የዙህርና የዐስር ሰላትን በዙህር ሰላት ወቅት (ወደ ሁለት ሁለት ረከዓ) በማሳጠር በአንድ አዛን እና ሁለት ኢቃማዎች ስገድ፡፡

- በዓረፋ ክልል ውስጥ መሆንህን አረጋግጥ የዓረፋ ምድር ሁሉ[1] መቆሚያ (መውቂፍ) ነውና፡፡ እንዲሁም የመልዕክተኛውን ሙስጠፋ (ﷺ) አርአያነት በመከተል አላህን ማወደስን (ዚክርን) እና ወደ ቂብላ አቅጣጫ በመዞር እጆችህን በማንሳትዱዓእ ማድረግን አብዛ፡፡ (በዚም ሁኔታህ) ፀሐይ እስክትጠልቅ በዐረፋ ክልል ቆይ፡፡

4. ፀሐይ ስትጠልቅ በሰከነ እና እርጋታ በተሞላበት ሁኔታ ተልቢያን እያደረግክ ወደ ሙዝደሊፋ ሂድ፡፡ ሙስሊም ወንድሞችህን (በመግፋት እና በመሳሰሉት) አታስቸግር፡፡ ሙዝደሊፋም ስትደርስ መግሪብ እና ዒሻእን በአንድ ወቅት (አራት ረከዓ የሆነውን) ወደ ሁለት ረከዓ በማሳጠር ስገድ፡፡ ከዚህ በኋላ ፈጅር እስክትሰግድ እና የፀሐይ መውጫ እስኪቃረብ (ጨለማው ተወግዶ ሰዎች መተያየት እስኪጀምሩ) በዚያ ትቆለህ፡፡ የፈጅር ሰላትን ከሰገድክ በኋላ የነብዩን (ﷺ) አርአያነት በመከተል፣ ወደ ቂብላ አቅጣጫ በመዞርና እጆችህን ወደ ላይ በማንሳት ዱዓእ እና ዚክር አብዛ፡፡

5. ፀሐይ ከመውጣቷም በፊት ተልቢያ እያደረከግክ ወደ ሚና መጓዝ ጀምር፡፡ ነገር ግን ሐጅ አድራጊው ከሴቶች፣ ከሕፃናት ፣ ከአካል ጉዳተኞች፣ ከአቅመ ደካሞች[2] በመሆኑ (ኋላ ሊከሰት የሚችለውን መጨናነቅ የማይቋቋምበት ምክንያት ያለው ከሆነ) ከለሊቱ አጋማሽ በኋላ ወደ ሚና

[1] የኡርናህ ሸለቆ ሲቀር

[2] ወይም ለአቅመ ደካሞች እንክብካቤ የሚያደርግ

ቢጓዝ ችግር የለውም፡፡ ጀምረቱል-ዓቀባ[1] ላይ ለመወርወር ሰባት ጠጠሮችን ብቻ ያዝ፡፡ ከዚህ ቀን ውጪ ለምታደርጋቸው የጠጠር ውርወራዎች ጠጠሮቹን ከሚና ትለቅማለህ (ሆኖም) ለዚህ ቀንም ቢሆን ጠጠሮቹን ከሚና መልቀምህ ችግር የለውም፡፡

6. ሚና ስትደርስ የሚከተሉትን ተግባራዊ አድርግ፡-

- ከመካ ይበልጥ ቅርብ በሆነችው ጀምረቱል-ዓቅባ ላይ እያንዳንዱን ጠጠር"አላሁ አክበር" እያልክ በተከታታይ ሰባት ጠጠሮችን ወርውር፡፡

- ለማረድ የምትገደድ(ሙተመቲዕ ወይም ቃሪን) ከሆንክ ሀድይህን እረድ፡፡ ከእርሱም ብላድሆችንም አብላ፡፡

- ፀጉርህን ተላጭ ወይንም አሳጥር፡፡ ሆኖም በዚህ ወቅት መላጨቱ የተሻለ ነው፡፡ ሴት ልጅ ግን የጣት አንጓ ያህል ታሳጥራለች፡፡

- ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ቅደም ተከተል የተሻለ እና በላጭነት ያለው ሲሆን አንዱን ከሌላኛው ብታስቀድምም ችግር የለውም፡፡

- ጀምረቱል-ዓቅባ ላይ ጠጠሮችን ከወረወርክ እና ፀጉርህን ከተላጨህ ወይንም ካሳጠርክ የመጀመሪያውን ተሀሉል አስገኘተሀልና ከዚህ በኋላ በኢሕራም የተነሳ የተከለከልካቸውን የልብስ ዓይነቶችንመልበስን ጨምሮ

---

[1] **ጀምረቱል-ዓቀባ፡-** ማለት በዒዱ ዕለት ሑጃጆች ጠጠር የሚወረውሩበት ብቸኛው ጠጠር መወርወሪያ ሲሆን እርሱም ለመካ የበለጠ ቅርብ የሆነው እና ጀምረቱል ኩብራ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡

ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጭሌሎቹነገሮች ባጠቃላይ ይፈቀዱልሀል፡፡

7. በመቀጠል ወደ መካ በመሄድ ጠዋፈል-ኢፋዳን[1] አድርግ፡፡ ሙተመቲዕ ከሆንክ ደግሞ ከጠዋፍ በኋላ ሳዕይን ጨምርበት፡፡ ነገር ግን ሐጅና ዑምራን አጣምረህ የምትፈፅም (ቃሪን) ወይም ሐጅን ብቻ የምታደርግ (ሙፍሪድ) ከሆንክ እና ከመግቢያ ጠዋፍ (ጠዋፍ አል-ቁዱም) በኋላ ሰዕይ አድርገህ ከነበረ አሁን ሰዕይ የለብህም፡፡ በዚህም ተግባረህ የግብረስጋ ግንኙነትን ጨምሮ በኢሕራም የተነሳ የተከለከልካቸው ነገራት ሁሉ ይፈቀዱልሀል፡፡

- ጠዋፈል-ኢፋዳን እና ሳዕይን ሚና ውስጥ ከሚቆይባቸው (ከዙልሒጃ 10-13) ቀናት በኋላ ማዘግየት ይቻላል፡፡

8. የእርዱ ዕለት ጠዋፈል-ኢፋዳ እና ሰዕይን ከፈፀምክ በኋላ ወደ ሚና ተመልሰህ እዚያው (ከዙልሒጃ ወር) አስራ አንደኛውን፣ አስራ ሁለተኛውን እና አስራ ሶስተኛውን (ሶስቱን የአያም-አተሽሪቅ ቀናት) ለሊቶች እደር፡፡ ሆኖም በአስራ ሁለተኛው ቀን (ከሚና ለመውጣት)ብትቻኮል እና ብትወጣ ችግር የለውም፡፡

9. በሁለቱ ወይም ሶስቱ በሚና በምትቆይባቸው ቀናትም ፀሐይ ከአናተ ካዘነበለች (ከእኩለ ቀን) በኋላ ሶስቱ የጠጠር መወርወሪያ ጉድጓዶች ላይ ጠጠር ወርውር፡፡ በመጀመሪያ ከመካ ይበልጥ እሩቅ በሆነችው ጉድጓድ ትጀምራለህ፡፡ ከዚያም በመሀከለኛው ትቀጥላለህ፡፡

[1] **ጠዋፈል ኢፋዳ** ከጠዋፍ አይነቶች እና ከአራቱ የሐጅ መዕዘናት አንዱ ሲሆን ሑጃጆች ከዙልሒጃ አስር ቀን ጀምሮ የሚፈፅሙት ታላቅ ዒባዳ ነው።

በመጨረሻምበጀምረቱል-ዓቅባታበቃለህ፡፡ በእያንዳንዱ ጉድጓድ ላይ ሰባት ጠጠሮችን፣በተከታታይ እና እያንዳንዱን ጠጠር ስትወረውር “አላሁ አክበር” እያልክ የጠጠር ውርወራህን ታከናውናለህ፡፡ የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ጉድጓድ ላይ ጠጠር ከወረወርክ በኋላወደ ቂብላ አቅጣጫ በመዞር እጅህን ወደ ላይ በማንሳት የፈለግከውን አላህን ትጠይቃለህ፡፡ ከጀምረቱል-ዓቀባ በኋላ ግን አትቆምም፡፡

- ሚና ውስጥ የመቆያህን ጊዜ በሁለት (በ11ኛው እና 12ኛው) ቀናት ከገደብከው የሁለተኛው ቀን ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ሚናን ለቀህትወጣለህ፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ በሚና ክልል ውስጥ ሳልህ ፀሐይ ከጠለቀችብህ ሶስተኛውን ቀን በዚያው ቆይተህ እንደ ሁለቱ ቀናት ሁሉ ጠጠርን ተወረውራለህ፡፡ሆኖም (ሚና ውስጥ የመቆያህን ጊዜ በሁለት ቀናት ከመገደብ ይልቅ) ሶስተኛውንም ለሊት በዚያው ማደርህ በላጭ ነው፡፡

- በሽተኞች እና አቅመ ደካሞች ጠጠርን በመወርወር ላይ ሌላ ሰው መወከል ይፈቀድላቸዋል፡፡ ተወክሎ ጠጠር የሚወረውረውም ሰው እንዱ በሄደበት በመጀመሪያ ለራሱ ከዚያም ለወከለው ሰው መወርወር ይፈቀድለታል፡፡

10. የሐጅን ስራ አጠናቀህ ወደ አገርህ መመለስ ስትፈልግ በካዓባ ዙሪያ የመሰናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፈል-ወዳዕን) አከናውን፡፡ ይህንን ጠዋፍ ሳያደርጉ ወደ አገር መመለስበወር አበባ እና በወሊድ ደም ላይ ካሉሴቶች ውጭለማንምአልተፈቀደም፡፡

# በሙህሪም ላይ ግዴታ የሚሆኑ ነገሮች

የሚከተሉት ነገሮች በሐጅም ይሁን በዑምራ ኢሕራም (ኒያ) ባደረገ ሰው ላይ ግዴታ ይሆናሉ፡-

1. ሰላትን በወቅቱ እና በጀመዓመስገድን የመሳሰሉ ሀይማኖታዊ ግዴታዎችን መወጣት፡፡

2. እንደየተቃራኒን ጾታ ስሜት ቀስቃሽ ንግግሮች እና ተግባራትን እንዲሁም የግብረ ስጋ ግንኙነት፣አመጽ፣ ክርክር እና ንትርክ ያሉ (በተለይ በሐጅ ላይ) አላህ የከለከላቸውን ነገሮች ሊርቅ ይገባል፡፡

3. በንግግርም ይሁን በተግባር ሙስሊሞችን ከማስቸገር ሊርቅ ይገባል፡፡

4. በኢሕራም የተነሳ የሚከለከሉ ነገሮችን (ማህዙራት አል-ኢሕራም) ሊርቅ ይገባል፡፡ እነርሱም፡-

- ከፀጉሩ ወይም ጥፍሩ ምንም አያስወግድም፤ ነገር ግን ከርሱ ፍላጎት ውጪ በራሱ ቢነቀል ወይ ቢቆረጥ ወንጀለኛ አይሆንም፡፡
- ሽቶን በሰውነቱ ፣ በልብሱ ወይም በመብሉ አልያም በሚጠጣው ነገር ላይ አይጠቀምም፤ ሆኖም ከኢሕራም በፊት የተጠቀመው ሽቶ ቅሪት ቢኖር ችግር የለውም፡፡
- ሙህሪም እስከሆነ (በኢሕራም ላይ እስካለ) ድረስየዱር እንስሳትን በመግደልም ይሁን በማስበርገግ አልያም ሌላን በዚህ (በአደን) ስራ ላይ የተሰማራን ሰው መተባበር አይችልም፡፡

- ሙህሪም በኢሕራም ላይ እስካለ ድረስ ለጋብቻ አያጭም ለራሱም ይሁን ለሌላ የጋብቻ ውል አይዋዋልም፣ ወሲባዊ ግንኙነትም አይፈፅምም እነዲሁም ሴቶችን በስሜት አይተሻሽም፡፡

  ከዚህ በላይ ያሳለፍናቸው (በኢሕራም የተነሳ የተከለከሉ ነገሮች) ወንዶችንም ይሁን ሴቶችን የሚመለከቱ ሲሆኑ የሚከተሉት ነጥቦች ደግሞ ወንዶችን ብቻ የሚመለከቱ ይሆናሉ፡-

- ከጭንቅላቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሚኖረው (እንደ ኮፊያ እና ጥምጣም ባለ) ነገር ራሱን አይሸፍንም፡፡ ነገር ግን በዣንጥላ ወይም የመኪና ጣራ አልያም በራሱ ላይ እቃን በመሸከሙ ቢጠለል ችግር የለውም፡፡

- (ሙህሪም) ቀሚስ እና መሰል (እንደ ኮት፣ ሸሚዝ፣ ከኔተራ እና ፓንት ያሉ)(በሰውነት አካላት ልክ) የተሰፋ ሙሉውን ወይም ከፊል አካልንየሚሸፍኑልብሶችንም ይሁን በርኖስን ዓማኢምን፣ሱሪን፣ከቁርጭምጭሚት በላይ የሆነ ጫማን(ኹፍን) አይለብስም፡፡ ነገር ግን የሚያሸርጠው ቢያጣ ሱሪ ወይም ከቁርጭምጭሚት በታች የሆነ ጫማ ቢያጣና ኹፍ ቢለብስ ችግር የለውም፡፡

- በኢሕራም ወቅት ሴት ልጅ በእጆቿ ላይ ጓንት ማጥለቅ፣ ፊቷን በኒቃብ ወይም በቡርቁዕ[1] መሸፈን ትከለከላለች፡፡

[1] **ቡርቁዕ እና ኒቃብ** በዚህ አገባብ መሰረት አንድ አይነት መልእክት የሚያስጨብጡ ቃላት ሲሆኑ እርሱም ሴት ልጅ ከአይን ውጭ ሌላውን የፊቷን ክፍል ለመሸፈን የምትጠቀምበት ጨርቅ ነው፡፡

ሆኖም ባዕድ (መህረሞቿ ያልሆኑ) ወንዶች ባሉበት ቦታ ፊቷን በሻሽዋ እና በመሳሰሉት ነገሮች መሸፈን ልክ በኢሕራም ላይ ከመሆኗ በፊት ግዴታ እንደነበር ሁሉ ግዴታ ይሆንባታል፡፡

- መሁሪሙ ረስቶ ወይም ባለ ማወቅ (በሰውነት አካላት ልክ) የተሰፋ ልብስን ቢለብስ ወይም ጭንቅላቱን (ከጭንቅላቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሚኖረው እንደ ኮፊያ እና ጥምጣም ባለ  ነገር) ቢሸፍን፣ ሽቶ ቢቀባ ፣ ከፀጉሩ አልያም ከጥፍሩ የተወሰነውን ቢያስወገድ የማካካሻ እርድ (ፊድያ) ግዴታ አይሆንበትም፡፡ ሆኖም ያ ድርጊት የተከለከለ መሆኑን ሲያስታውስ ወይም ሲያውቅ ከድርጊቱ መቆጠብ ግዴታ ይሆንበታል፡፡
- ከቁርጭምጭሚት በታች የሆነ ጫማ ፣ ቀለበት፣ መነፅር፣ ማዳመጫ፣ ሰዓት፣ቀበቶ ፣ ገንዘብ እና ወረቀቶች መያዣ ቦርሳ መጠቀም ይፈቀዳል፡፡
- ልብስን መቀየር፣ማጠብ፣ራስን እና መላ ሰውነትን መታጠብ ይፈቀዳል፤ ሆን ብሎ ሳይሆን በዚህ የተነሳፀጉሩ ቢነቀል(ቢሰበር) እንዲሁም ቁስለት ቢገጥመውችግር የለውም፡፡

# የመልዕክተኛው (ﷺ) መስጅድ ጉብኝት አፈፃፀም

1. የነብዩን (ﷺ) መስጅድ ለመጎብኘት እና በውስጡ ሰላትን ለመስገድ በማሰብ ወደ መዲና ከተማ በማንኛውም ወቅት መሄድ ሱና (የተወደደ) ነው፡፡ ምክንያቱም በመስጅድ አን-ነበዊ ውስጥ የሚሰገድ ማነኛውም ሰላት ከመስጂደል-

ሀራም ውጭበሌሎቹ መስጂዶች ከሚሰገደው ምንዳው በአንድ ሺህ እጥፍ ይበልጣልና፡፡

2. የነብዩን (ﷺ) መስጅድ ለመጎብኘት ኢሕራምም ይሁን ተልቢያ የለውም፡፡ እንዲያውም በሐጅ እና በእርሱ መካከል ፈፅሞ ግንኙነት የለም፡፡

3. መስጂድ አን-ነበዊ ስትደርስ በሌሎች መስጅዶች መግቢያ ላይ እንደተደነገገው ቀኝ እግርህን በማስቀደም "ቢስሚላሂ ወሰላቱ ወስላሙ ዓላ ረሱሊላህ" በማለት የአላህ ሰላት እና ሰላም በነብዩ ላይ እንዲሰፍን እንዲሁምየእዝነቱን (የራህመቱን) በር እንዲከፍትልህ አላህን እየለመንክ፣ በተጨማሪም

أعوذ بالله العظيم , وبوجهه الكريم, وسلطانه القديم, من الشيطان الرجيم

اللهم افتح لي أبواب رحمتك

**"አዑዙ ቢላሂ አልዐዚም ወወጅህሂ አልከሪም ወሱልጣኒሂ አልቀዲም ሚነ አሸይጣን አረጂም፡፡ አላሁም ኢፍታህሊ አብዋበ ረህመቲክ"** በማለት ግባ፡፡

**ትርጉሙም፦** «የላቀ በሆነው አላህ በተከበረው ፊቱ ጥንታዊ በሆነው ስልጣኑ እርጉም ከሆነው ሰይጣን እጠበቃለሁ፡፡»«አላህ ሆይ!የእዝነት በሮችህን ክፈትልኝ፡፡ »(የመጀመሪያውን አቡዳውድ ቀጣዩን ሙስሊም ዘግበውታል)

4. እንደገባህም "ተሂየተል-መስጂድን"ከተመቸ ረውዳው ላይ ብትሰግድ የተሻለ ነው፡፡ ካልሆነም በመስጅዱ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ስገድ፡፡

5. በመቀጠል ወደ ነብዩ (ﷺ) ቀብር በመሄድወደ እርሱ ዞረህ ቁም፡፡ በስርአት እና ድምፅህን ዝቅ በማድረግ

السَّلاَمُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِىُّ وَرَحْمَةُ اللَّهِ وَبَرَكَاتُهُ

**"አሠላሙ ዓለየከ አዩሀ አንነብዩ ወራህመቱላሂ ወበረካቱህ"** በል፡፡

**ትርጉሙም፦** «አንተ ነብይ ሆይ! የአላህ ሰላም፣እዝነት እና በረከት በእርሶ ላይ ይሁን»

የአላህ ሰላትም (ውዳሴም) በእርሳቸው ላይ እንዲሆን አላህን ለምን፡፡ በተጨማሪም

اللهم آته الْوَسِيلَةَ وَالْفَضِيلَةَ وَابْعَثْهُ الْمَقَامَ الْمَحْمُودَ الَّذِي وَعَدْتَهُ. اللهم اجزه عن أمته أفضل الجزاء

**"አላሁመ አቲሂ አልወሲለተ ወልፈዲለተ ወብዓስሁ አልመቃም አልመህሙድ አለዚ ወዐድተሁ፡፡ አላሁመ እጅዚሂ ዓን ዑመቲሂ አፍደለልጀዛእ"** ማለትህ ችግር የለውም፡፡

**ትርጉሙም:-** «አላህ ሆይ! ለነብዩ "ወሲላ" የተባለውን ጀነት እና ታላቅ የሆነውን ደረጃ ስጣቸው፡፡ ቃል የገባህላቸውንም ምስጉን ስፍራ አጎናጽፈህ ቀስቅሳቸው፡፡ ለኡመታቸው በዋሉትም መልካም ውለታከሁሉ የተሻለ የሆነውን (መልካሙን) ምንዳ መንዳቸው»

- ከዚያም ጥቂት ወደ ቀኝ ፈቅ ብለህ ከአቡበክር (አላህ ስራቸውን ይውደድላቸው) ቀብር ፊት ለፊት ትቆማለህ፡፡

ሰላምታን ታቀርባለህ፣ለእርሳቸውም የአላህን ምህረት፣ እዝነት እና ውዴታን ትለምናለህ፡፡

- በድጋሚ ጥቂት ወደ ቀኝ ፈቅ ብለህ ከዑመር (አላህ ስራቸውን ይውደድላቸው) ቀብር ፊት ለፊት ትቆማለህ፡፡ ሰላምታን ታቀርባለህ፣ለእርሳቸውም የአላህን ምህረት፣ እዝነት እና ውዴታን ትለምናለህ፡፡

6. ነብዩ (ﷺ) ያደርጉት እንዲሁም ሰዎችንምእንዲያደርጉት ያነሳሱ የነበረ ከመሆኑ አንፃር ውዱእ አድርገህ ወደ መስጂድ ቁባእ በመሄድ ብትጎበኘው በውስጡም ብትሰግድ ይወደድልሃል (ሱና ይሆንልሃል)፡፡

7. የዑስማን (አላህ ስራቸውን ይውደድላቸው) ቀብር ያለበትን የበቂዕን መካነ መቃብር እና ከመካከላቸው አንዱ ሀምዛ (አላህ ስራቸውን ይውደድላቸው) የሆኑትን የኡሁድ ሰምዓታት መካነ መቃብር በመጎብኘት ሰላምታን ብታቀርብላቸው እንዲሁም ዱዓእ ብታደርግላቸው ይወደድልሀል (ሱና ይሆንልሀል)፡፡ ምክንያቱም ነብዩ (ﷺ) ይጎበኟቸው እና ዱዓእ ያደርጉላቸው ነበርና፡፡ ባልደረቦቻቸውንም ቀብርን በሚጎበኙበት ወቅት እንዲህ እንዲሉ አስተምረዋል፡-

السَّلاَمُ عَلَيْكُمْ أَهْلَ الدِّيَارِ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُسْلِمِينَ إِنَّا إِنْشَاءَ اللَّهُ بِكُمْ لاَحِقُونَ نَسْأَلُ اللَّهَ لَنَا وَلَكُمُ الْعَافِيَةَ

**“አሰላሙ ዓለይኩም አህለ አዲያር ሚነል ሙእሚኒነ ወል ሙስሊሚን ወኢና ኢንሻ አላሁ ቢኩም ላሂቁን ነስአሉላሀ ለና ወለኩሙል ዓፊየተ”**

**ትርጉሙም፦**«በዚህ መካነ መቃብር ውስጥ ያላችሁ ሙእሚኖችና ሙስሊሞች ሆይ! ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፡፡ እኛም በአላህ ፍቃድ የእናንተ ተከታዮች ነን፡፡ ለእኛ እና ለእናንተም ከአላህ ደህንነትንእንለምናለን፡፡» (ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

- ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውጭ በመዲና ከተማ ውስጥ በሸሪዓ መጎብኘታቸው የተደነገገ ሌሎች መስጂዶችም ይሁን ቦታዎች የሉም፡፡ ስለዚህም አንዳች ምንዳን የማያስገኝልህን ምናልባትም (እርሱን ለመጎብኘት በምታደርገው እንቅስቃሴ)ወንጀለኛልትሆን የምትችልበትን ተግባር በመፈጸም እራስህን አታስቸግር፡፡ስኬታማ የማድረግ ስልጣን የአላህ ነው፡፡

# አንዳንድ ሑጃጆች የሚፈፅሟቸው ስህተቶች

**በመጀመሪያ፡- በኢሕራም ወቅት የሚስተዋሉ ስህተቶች፦**

1. ኢሕራም (ኒያ) ሳያደርጉ በሚመጡበት አቅጣጫ ያለውን ኢሕራም ማድረጊያ ስፍራ (ሚቃት) አልፎ ከሚቃት ክልል ውስጥ ካሉ እንደ ጅዳ እና መሰል ከተሞችመድረስ ከዚያም ስፍራ ኢሕራም (ኒያ) ማድረግ፡፡ ይህ ድርጊት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እያንዳንዱ ሑጃጅ ከሚመጣበት አቅጣጫ ሚቃት ኢሕራም እንዲያደርግ ያስተላለፉትን ትዕዛዝ የሚቃረን ነው፡፡

2. በአየርም ይሁን በምድር አልያም በባህር ሚቃትን አልፎ የመጣ ሰው ከቻለ ወደዛው ተመልሶ ኢሕራም (ኒያ) ማድረግ ግዴታ የሚሆንበት ሲሆን ካልቻለ ግን የማካካሻ

እርድ (ፊድያ) መካ ውስጥ እርዶ ሁሉንም ለምስኪኖች ማብላት ግዴታ ይሆንበታል፡፡

3. ከአምስቱ ኢሕራም(ኒያ) ማድረጊያ ስፍራዎች በአንዱም ያላለፈ (ሐጅን ወይም ዑምራን ማድረግ የሚያስብ)ሰው ከሚመጣበት አቅጣጫ በመጀመሪያ በሚያገኘው ሚቃት አኳያ (ትይዩ) ሲሆን ኢሕራም (ኒያ) ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

**ሁለተኛ፡- በጠዋፍ ላይ የሚስተዋሉ ስህተቶች፡-**

1. ከሀጀረል-አስወድ በፊት ጠዋፍን መጀመርስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛው እናግዴታም የሚሆነው ጠዋፍን ከሀጀረል-አስወድ መጀመር ነውና፡፡

2. ጠዋፍን በካዕባ ሂጅር(1) ውስጥ ማድረግስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ጠዋፍ ካዕባን ሙሉ በሙሉ ያካለለ አይደለም፡፡ ይሉቁኑ ሂጅሩ ከካዕባው ክፍል ስለሆነ በካዕባ መሃል እንደተደረገ ነው የሚቆጠረው፡፡በመሆኑም (ጠዋፍ አድራጊው) ከሂጅር ውስጥ በማለፍ ያደረገው የጠዋፍ ዙር ውድቅ ይሆናል፡፡

3. ረመልን (ማለትም እርምጃን ከማቀራረብ ጋር መፍጠንን) በሰባቱም (የጠዋፍ) ዙሮች ላይ ማድረግስህተት ነው፡፡ ይህ (ድርጊት) ከመግቢያ ጠዋፍ (ጠዋፈል-ቁዱም)*የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ዙሮች ላይ ብቻ የሚፈፀም ነው፡፡

4. ሀጀረል-አስወድን ለመሳም ሲባልመገፋፋት አልፎ አልፎም መመታታት እና መሰዳደብ ስህተት ነው፡፡ ይህ ሙስሊሞችን ማስቸገር ከመሆኑም አንጻር አይፈቀድም፡፡

በተጨማሪም አንድ ሙስሊም ወንድሙን ያለ አግባብመስደብምይሁን መምታት ፈጽሞ አይፈቀድለትም፡፡

- ሀጀረል-አስወድን አለመሳም ጠዋፍን አያጎድልም፤ ይልቅ አንድ ጠዋፍ አድራጊ ሀጀረል አስወድን ባይስምም እንኳ ጠዋፉ ትክክለኛ ነው፤እርቀት ላይ እንኳ ቢሆን በእርሱ ትይዩ ሲሆን እጁን ማንሳቱ እና “አላሁ አክበር” ማለቱ ይበቃዋል፡፡

5. ረድኤትን(በረከትን) ለመጎናፀፍ በማሰብ ሀጀረል-አስወድን መተሻሸትስህተት ነው፡፡ ይህ በሸሪዓ መሰረት የሌለው የፈጠራ (የቢድዓ) ተግበር ሲሆን ሱናውወደ አላህ መቃረብን በማሰብ እርሱን ሰላም ማለት እና መሳም* ነው፡፡

6. ሁሉንም የካዕባ መአዘናት ምን አልባትም ግድግዳዎቹን ሁሉ ሰላም ማለት (ኢስቲላም ማድረግ) እና መተሻሸትስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ነብዩ (ﷺ) ከካዕባ መአዘናት ሀጀረል-አስወድንና አሩክነል-የማኒንእንጂ ሌላን ሰላም አላሉም፡፡

7. እያንዳንዱን የጠዋፍ ዙር እራሱን በቻለ የዱዓእ አይነት መለየት (ስህተት ነው)፡፡ ምክንያቱም ይህ አይነቱ ተግባር ከነብዩ (ﷺ) አልተገኘምና፡፡ ይልቁኑ ነብዩ (ﷺ) በጠዋፍ ላይ ሀጀረል-አስወድ ጋር ሲደርሱ “አላሁ አክበር” ይሉ በእርሱ እና በሩክነል-የማኒ መካከል ሲሆኑም ይህንን ዱዓዕ ያደርጉ ነበር፡-

رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

**"ረበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበ-ንናር"**

ትርጉሙም፦«ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን»

8. ከአንዳንድ ጠዋፍ አድራጊዎች ወይም ጠዋፍ "አስደራጊዎች" በጠዋፍ ወቅት የሚስተዋል ሌሎች ጠዋፍ አድራጊዎችን በሚረብሽ መልኩ ድምፅን ከፍ የማድረግ ክስተትስህተት ነው፡፡

9. መቃመ ኢብራሂም ጋር ለመስገድ ሲባል የሚከሰት ሰዎችንየመግፋት(የማጨናነቅ) ድርጊት (ስህተት ነው)፡፡ ድርጊቱ ጠዋፍ አድራጊዎችን ማስቸገር ከመሆኑም ባሻገር ከሱና ተቃራኒ ነው፡፡ ጠዋፍ አድራጊውከጠዋፍ በኋላያለውን ሁለት ረከዓ ሰላት ከመስጅዱ በማንኛውም ስፍራ መስገድ ይችላል፡፡

**ሦስተኛ፡- በሰዕይ ወቅት የሚስተዋሉ ስህተቶች**

1. አንዳንድ ሑጃጆች ወደ ሰፋ እና መርዋኮረብታዎች ሲወጡ ወደ ካዕባ በመዞር ልክ ለሰላት መግቢያ ("ተክቢረተል-ኢሕራም" የሚያደርጉ ይመስል) "አላሁ አክበር"እጃቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ አለ ይህ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ቦታ ላይ ሱናው ልክ ዱዓእ እንደሚያደርግ ሰው ሁለት እጆችን ወደ ላይ ማንሳት ነው፡፡

2. በሰፋ እና መርዋ መካከል በሚደረገው ምልልስ ዙሩን ሙሉከጫፍ እስከ ጫፍመሮጥስህተት ነው፡፡ በዚህ ቦታ ሱናው በሁለቱአረንጓዴ ምልክቶች መካከል መፍጠን

(መሮጥ) እና ቀሪዎቹን (ከምልክቶቹ በፊት እና በኋላ ያሉትን) ርቀቶች በተለመደው እርምጃ በመራመድ ማሟላት ነው፡፡

**አራተኛ፡- በዓረፋት የሚስተዋሉ ስህተቶች፡**

1. አንዳንድ ሑጃጆች ከዓረፋ ክልል ውጪ ሰፍረው ፀሐይ እስክትጠልቅ በዚያው በመቆየት ወደ ዓረፋ ክልል ሳይገቡ(ዓረፋ ላይ ሳይቆሙ) በዚያው ወደ ሙዝደሊፋ መመለሳቸው ሐጃቸውን ውድቅ የሚደርግባቸው እጅግ የከፋ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ሐጅ ማለት በዓረፋምድር መገኘት ነውና፡፡ ስለሆነምሑጃጆች ከዓረፋ ክልል ውስጥ መሆን ግዴታቸው ነው። ይህንንም ለማድረግ የቻሉትን ጥረት ሊያደርጉ ይገባቸዋል። ሆኖም ይህንን ማድረግ ካልቻሉ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ገብተው እስክትጠልቅ መቆየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ (በተለያዩ ምክንያቶች) በዓረፋ ምድር የቀኑን ክፍለ ግዜ ማሳለፍ ላልቻሉ ሰዎች ብቻለሊቱን (ማለትም የዓረፋን ቀን ማምሻ)በዓረፋ ክልል መገኘት ያብቃቃቸዋል።

2. አንዳንድ ሑጃጆች ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የዓረፋን ክልል ለቀው መውጣታቸውስህተት ነው፡፡እንዲያውም ይህ ድርጊት የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በዓረፋ ምድር ሙሉ ለሙሉ ፀሐይ እስክትጠልቅ ቆይተዋልና፡፡

3. ወደ ዓረፋ ተራራ ለመውጣት ብሎም እጫፉ ለመድረስ ሲባል የሚከሰት ትርምስ እና መጨናነቅ፡፡ይህ ከፍተኛ ጉዳትየሚያስከትል ስህተት ነው፡፡ የዓረፋ ምድር ሁሉ መቆሚያ (መውቂፍ) ነው፡፡ነገር ግን ወደ ተራራው

መወጣት እንዲሁም እርሱ ላይ ሰላት መስገድ በሸሪዓመሰረት ያለው አይደለም፡፡

4. አንዳንድ ሑጃጆች ለዱዓእ ወደ ዓረፋ ተራራ መዞራቸውስህተት ነው፤ ይልቅሱናው ለዱዓእ ወደ ቂብላ (ካዕባ) አቅጣጫ መዞር ነው፡፡

5. አንዳንድ ሑጃጆች በዓረፋ እለት (ከዙልሒጃ ዘጠነኛው ቀን ማለት ነው) በተወሰኑ ቦታዎች አፈር እና ጠጠሮችን የመሰብሰብእና የማከማቸት ሁኔታ በሸሪዓ ምንም አይነት መሰረት የሌለውተግባር ነው፡፡

## አምስተኛ፡- ሙዘዝደሊፋ ላይ የሚስተዋሉ ስህተቶች

1. አንዳንድ ሑጃጆች መግሪብ እና ኢሻዕን ከመስገዳቸው በፊት ገና ሙዝደሊፋ እንደገቡ እራሳቸውን ጠጠር በመልቀም ስራ ላይ መጥመዳቸው፤በተጨማሪም በመወርወሪያ ጉድጓዶቹ ላይ የሚወረወሩት ጠጠሮች የግድ ከሙዝደሊፋየተለቀሙ መሆን አለባቸው ብለው ማመናቸው ስህተት ነው፡፡

2. በዘህ ጉዳይ ላይ ትክከለኛው አቋም ከየትኛውም የሀረም ክልል ጠጠሮቹን መልቀሙየሚቻል መሆኑ ነው፡፡ ከነብዩም (ﷺ) በትክክለኛ ሰነድ የተረጋገጠው ሀዲስ የሚጠቁመው እርሳቸው ጀምረተል-ዓቅባ ላይ የሚወረውሯቸውንጠጠሮች ከሙዝደሊፋ እንዲለቀሙላቸው አለማዘዛቸውን እና በንጋታው ከሙዝደሊፋ ሲመለሱ ሚና ከገቡ በኋላ እንደተለቀሙላቸው ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በቀሪዎቹ ቀናት የሚወረውሯቸውን ጠጠሮቸ ከሚና ነበር የለቀሙት (ያስለቀሙት)፡፡

3. አንዳንዶቹ ሑጃጆች ደግሞ ጠጠሩን በውሃ የሚያጥቡበት ሁኔታም ይስተዋላል ይህም በሸሪዓ ያልተደነገገ ተግባር ነው፡፡

**ስድስተኛ፡- በጠጠር ውርወራወቅት የሚስተዋሉ ስህተቶች፡**

1. አንዳንድ ሑጃጆች ጠጠር በሚወረውሩበት ወቅት ሸይጣንን ነው የምንወግረው በሚል እምነት ቁጣ በተሞላበት እና ስድብ በተቀላቀለበት ሁኔታ ጠጠሮቹን መወርወራቸው ነው፡፡ ነገር ግን ጠጠር የመወርወሩ ሂደት የተደነገገው አላህን ለማስታወስ እንጂ ለሌላ አይደለም፡፡

2. ሌላው ስህተት ደግሞ ጠጠሮችን በመወርወር ፈንታ (ከፍ ያሉ)ድንጋዮችን ወይም ጫማ አልያም እንጨቶችን መወርወር ነው፡፡ይህ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) የከለከሉት በዲን(በሀይማኖት) ድንበር ማለፍ ከመሆኑም ባሻገርግለሰቡ ከጠጠር ውርወራ አንጻር የሚጠበቅበትን ግዴታ ተወጥቷል የሚያሰኘው አይደለም፡፡

- ጠጠር መውርወሪያ ጉድጓዶቹ ላይ መወርወር የተደነገገው ትናናሽ የባቄላ ፍሬ የሚያካክሉ አልያም የትንሽ በግ ወይም ፍየል አይነምድርየሚስተካከሉ ጠጠሮችን መወርወር ነው፡፡

3. በጠጠር መወርወሪያዎቹ አካባቢ ጠጠር ለመወርወር ሲባል የሚከሰት መጨናነቅ እና ትንቅንቅ (ትግል)ስህተት ነው፡፡(በተለየ መልኩ እዚህ ቦታ ላይ) በሸሪዓ የተደነገገው ለሰዎች በማዘን እና በቻሉት አቅም ማንንም ሳያስቸግሩ የጠጠር ውርወራውን አጠናቆ(በጥንቃቄ) ወደ መጡብት መመለስነው፡፡

4. ጠጠሮቹን ሁሉ በአንድግዜ በአንድ ላይ መወርወር ስህተት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የእውቀት ባለቤቶች (ዑልማዎች) እንደ አንድ ጠጠር ብቻ የሚታሰብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

- (ጠጠር አወራወሩን በተመለከተ በሸሪዓ የተደረገገው) እያንዳንዱን ጠጠር ‹‹አላሁ አክበር›› ከማለት ጋር ተራ በተራ መወርወር ነው፡፡

5. ግፊያና ድካምን በመፍራት ጠጠር ለመወርወር አቅሙ እያለ ሌላን ሰው መተካት (መወከል) ስህተት ነው፡፡ በመሰረቱ ሰውን መተካት (መወከል) የሚቻለው በበሽታ እና መሰል ምክንያቶች አቅም ሲያንስ ብቻ ነው፡፡

**ሰባተኛ፡- ከመሰናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፈል-ወዳዕ) ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ስህተቶች፡-**

1. አንዳንድ ሑጃጆች በመጨረሻው ቀን ጠጠር ከመወርወራቸው በፊት ከሚና መካ በመሄድ የመሰናበቻ ጠዋፍን አድርገው ወደ ሚና ተመልሰው ጠጠር መወርወራቸው ከዚያም ከዚያው ወደ አገራቸው መጓዛቸውስህተት ነው፡፡ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ከሐጅ ስራ በኋላ ስንብታቸውከጠጠር መወርወሪያዎቹእንጂ በካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ በማድረግ አልሆነምና፡፡ይህን በማስመልከት ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

لاَ يَنْفِرَنَّ أَحَدٌ حَتَّى يَكُونَ آخِرُ عَهْدِهِ بِالْبَيْتِ

«አንዳችሁ (ከሐጅ ስራ በኋላ) ወደ አገሩ (መካን) ለቆ መሄድ የለበትም የመሰናበቻው (ማሳረጊያው) ተግባር

በአላህ ቤት (ካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ) ቢሆን እንጂ» (ሙስሊም ዘግበውታል)

- ስለሆነም የመሰናበቻው ጠዋፍ ከሐጅ ሰራ በኋላ ለጉዞ ጥቂት ሲቀር መሆኑ ግዴታ ነው፡፡ (ሐጃጁ ከዚያ በኋላ) ምናልባት ብዙ ጊዜ የማይወስዱ አጋጣሚዎች እስካልተፈጠሩ ድረስ በመካ ከተማ ውስጥ አይቆይም፡፡

2. ከመሰናበቻው ጠዋፍ በኋላ ካዕባንማክበር ነው በሚል የተሳሳተ እምነት(ግምት) ፊትን ወደ ካዕባ አዙሮ የኋልዮሽ ከመስጂድ መውጣት፡፡ ይህ በዲን መሰረት የሌለው የፈጠራ (የቢድዓ) ተግባር ነው፡፡

3. የመሰናበቻ ጠዋፍን ከጨረሱ በኋላ መስጂደል ሀራም በር ላይ ደርሶ ወደ ካዕባ በመዞር ካዕባን ይሰናበቱ ይመስል የተለያዩ ዱዓኦችን ማድረግ ስህተት ሲሆን ይህም እንደመጀመሪው ሁሉ በሸሪዓ ያልተደነገገ የፈጠራ ተግባር ነው፡፡

**ስምንተኛ፡- በመስጅድ አን-ነበዊ ጉብኝት ወቅት የሚስተዋሉ ስህተቶች፦**

1. የመልዕክተኛውን (ﷺ) ቀብር በሚጎበኙበት ወቅት ከግድግዳው እና ከብረት ዘንጎቹ ጋር በመተሻሸት እንዲሁም ክርና መሰል ነገሮችን በመስኮቶቹ ላይ በማሰር በረከትን(በረካን) እንጎናፀፋለን ብሎ ማሰብ ነው፡፡እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው በረካን ማግኘት የሚቻለው አላህና መልዕክተኛው (ﷺ) በደነገጉት (ህግ) እንጂ በፈጠራ (ቢዳዓ) አለመሆኑነው፡፡

2. በኡሁድ ተራራ ወደሚገኙ የተለያዩ ዋሻዎች በተመሳሳይ ሁኔታም መካ ውስጥ ወደ ሚገኙ "ሂራእ" እና "ሰውር" ወደተባሉ ዋሻዎች በመሄድ እነርሱምላይ ቁርጥራጭ ጨርቆችን ማሰርናበሸሪዓ መሰረት የሌላቸውንየተለያዩ ዱዓዎች ማድረጉ፣ ለዚህም ሲባል ያላግባብ እራስን ማስቸገሩ ስህተት ነው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተግባራት በአጠቃላይ በትክክለኛውየሸሪዓ ሕግ መሰረት የሌላቸው የፈጠራ (የቢድዓ) ተግባራት ናቸው።

3. የመልዕክተኛው (ﷺ) ዱካዎች አርፈውባቸዋል በሚልእንደ የመልዕክተኛው ግመል ያረፈችበት ቦታን የመሰለ እንዲሁም የዑስማን የውሀ ጉድጓድ በመባል የሚታወቀውን (የመልዕክተኛው (ﷺ)) ቀለበት ወድቃበታለች ወደሚባለው ጉድጓድ) በመሄድበረካን ለማግኘት ሲባል አፈራቸውን መውሰድ ስህተት ነው።

4. የበቂዕን እና የኡሁድ ሰምአታት መካነ መቃብርን ለመጎብኘት ሄዶ ሙታኖችን መለመን፣ ወደ እነርሱ ለመቃረብ እና ከእነርሱበረካን ለማግኘት ሲባል የተለያዩ የገንዘብ ኖቶችን (ብር እና ሳንቲሞችን) እዚያ ስፍራ መወርወር እጅግ ከገዘፉ ስህተቶች መካከል ነው። አንዲያውም የእውቀት ባለቤቶች እንደሚያወሱትየኪታብ እናየሱንና መረጃዎች እንደሚጠቀሙት ከትልቁ የሽርክ አይነት የሚመደብ ነው። አምልኮ ለአላህ ብቻ የሚገባ ነውና እንደ ዱዓእ፣ እርድ፣ስለት እና የመሳሰሉ (የአምልኮ ክፍሎችን) ከአላህ ሌላ ለማንም (ማዋል) መስጠት አይፈቀድም።ምክንያቱም አላህ (ﷻ) እንዲህ በማለቱ ነው፦

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ ﴾ البينة: ٥

**ትርጉሙም፦** «አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት... እንጅ አልታዘዙም፡፡»{አል-ብይናህ :5}

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَأَنَّ ٱلْمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدًا ﴿١٨﴾ ﴾ الجن: ١٨

**ትርጉሙም፦** «እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፡፡ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፡፡»{አል-ጂን :18}

አላህን የሙስሊሞችን ሁኔታ እንዲያስተካክል፣በእምነታቸው ላይ ሰፊ ግንዛቤን እንዲሰጣቸው፣ ሁላችንንም አጥማሚ ከሆኑ ፈተናዎች እንዲጠብቀን እንለምነዋለን፡፡ እነሆ እርሱም (ልመናን) ሰሚና ተቀባይ (ምላሽ ሰጪ ነው) ነው፡፡

# ወሳኝና አጭጭር ማሳሰቢያዎች ለሐጅ እና ዑምራ አድራጊዎች እንዲሁም የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጂድ ጎብኚዎች

- ሐጅ በሚያደርግ ሰው ላይ ተከታዮቹ ነጥቦች ግዴታ ይሆናሉ፡-

1. በአስቸኳይ ከሁሉም ወንጀሎች በትክክል ወደ አላህ መመለስ (ተውበት) ማድረግ፡፡ እንዲሁም ለሐጅ እና ዑምራው ማስፈፀሚያ ንፁህ (ሐላል) ገንዘብ መርጦመጠቀም ግዴታ ይሆንበታል፡፡

2. ምላሱን ከውሸት፣ከሀሜት፣ወሬን ከማሳበቅ (ማቃጠር) እና በሰዎች ላይ ከማፌዝ ሊጠብቅ (ግዴታ ይሆንበታል)፡፡

3. ሐጅና ዑምራውን ሲያደርግ ከይዩልኝ፣ ይስሙልኝ እና ዝናን ማትረፍን ከመፈለግ ርቆ የአላህን ፊት እና ዘላለማዊውን የወዳያኛው አለም ስኬት በመሻት ሊሆንይገባል፡፡

4. በሐጅና ዑምራ ውስጥ መፈፀም ያለበትን ንግግራዊ እና ተግባራዊ ስራዎች ሊማር፤ግልፅ ያልሆነለትንም ሊጠይቅ (ግዴታ ይሆንበታል)፡፡

5. ሐጃጁ ወደ ሚቃት ሲደርስ (ከሶስቱ የሐጅ እና ዑምራ አፈፃፀም ስርዓቶች) ኢፍራድ፣ተመቱዕ እና ቂራን የፈለገውን መምረጥ የሚችል ሲሆን ሆኖም ሀድይን እየነዳ (ይዞ) ካልመጣ በተመቱዕ፣ ሀድይን እየነዳ (ይዞ) ከመጣ ደግሞ በቂራን ስርዓት (ሐጅና ዑምራውን) ማድረጉበላጭነት አለው፡፡

6. በበሽታ ወይም(በመንገድ ላይ ሊከሰት በሚችል) ችግር ምክንያንትየሐጅን ወይም ዑምራን ስርአት ሙሉ በሆነ መልኩ ላልወጣ እችላለሁ ብሎከጅምሩ ስጋት የገባው ሙህሪም (ኒያውን በሚያደርግበት ወቅት) «(አንዳች እክል ገጥሞኝ የሐጅን ስራ ከመጨረስ ከታገድኩኝ) መፈቺያዬ (ማሳረጊያዬ) እዚያው የታገድኩበት ቦታ ነው፡፡» ብሎ ቅድመሁኔታን ማስቀመጥ ይችላል፡፡

7. የሕፃናት ሐጅ ምንም እንኳ ተቀባይነት ያለው ቢሆንምነገር ግን (በዚህ ጨቅላ እድሜ የፈፀሙት ሐጅ) በእያንዳንዱ ለአካለ መጠን በደረሰና አቅሙ ያለው ሙስሊም ላይ ያለውን ሐጅ የማድረግ ግዴታ እንደተወጡ አያስቆጥራቸውም፡፡

8. ሙህሪም ገላውን ሊታጠብ፣ራሱን (ፀጉሩን) ሊያጥብ ማከክ ካስፈለገውም ራሱን ሊያክይፈቀድለታል፡፡

9. ሙህሪም ሴት መህረሞቿ ያልሆኑ (ባዕድ) ወንዶች እንዳያይዋት ከሰጋች ሻሽዋን በፊትዋ ላይ ልትለቀው ይፈቀድላታል፡፡

10. ብዙ ሴቶች ከፊታቸው ላይ የለቀቁትን ሻሽ ፊታቸውን እንዳይነካ ከፍ ለማድረግ ከታቹ መደገፊያ የመሸጎጥ ልምድ በሸሪዓ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

11. ሙህሪም ኢሕራም ያደረገበትን ልብስ አጥቦ በድጋሚ መልበስ እንዲሁም በሌላ መቀየር ይፈቀድለታል፡፡

12. ሙህሪሙ ረስቶ ወይም ባለማወቅ (በሰውነት አካላት ልክ) የተሰፉ ልብሶችን ቢለብስ ወይም ጭንቅላቱን(ከጭንቅላቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሚኖረውእንደ ኮፊያ እና ጥምጣም ባለ ነገር) ቢሸፍን አልያም ሽቶን ቢጠቀም የማካካሻ እርድን (ፊድያን) ማረድግዴታ አይሆንበትም፡፡

13. ሐጃጁ ሙተመተዕ ወይም ዑምራ አድራጊ ከሆነ ወደ ካዕባ ሲደርስ ጠዋፉን ከመጀመሩ በፊት ተልቢያን ያቋርጣል፡፡

14. ረመልም ይሁን ኢድጢባዕ ከመግቢያ ጠዋፍ ውጭ በሌሎቹ የጠዋፍ አይነቶች የተደነገጉ አይደሉም፡፡ በተጨማሪም ረመል ከጠዋፉ በመጀመሪዎቹ ሶስቱ ዙሮች ላይ ብቻ የተደነገገ ሲሆን ሁለቱም ወንዶችን እንጂ ሴቶችን የሚመለከቱአይደሉም፡፡

15. ሐጃጁ (ጠዋፍ በማድረግ ላይ ሳለ) ስንት ዙር ነው ያደረግኩበት ብሎ ቢጠራጠር ለምሳሌ ሶስት ይሁን አራት

ዙር ጠዋፍ ያደረገው ግር ቢለው ሶስትአድርጎ በማሰብ የቀረውን ያሟላል፡፡ ሰዕይም ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ ቢገጥመው በተመሳሳይ ሁኔታ መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

16. (በጠዋፍ ላይ) መጨናነቅ በሚከሰትበት ወቅት ከዘምዘም ውሀ (መፍለቂያ) እና መቃመ ኢብራሂም ኋላ ጠዋፍ ማድረግ ችግር የለውም፡፡ የመስጅዱ የምድሩም ይሁን የፎቁ ክፍሎች ባጠቃላይ ጠዋፍ ማድረጊያ ናቸው፡፡

17. ጠዋፍ ላይ ከሚስተዋሉ የተኮነኑ የወንጀል ተግባራት መካከል አንዱ አንዲት ሴት ጌጦቿን ተጋጊጣ፣ጥሩ መዓዛ ያላቸውን ሽቶዎች ተጠቅማ እና ተገላልጣ ጠዋፍ ማድረጓ ነው፡፡

18. አንዲት ሴት ኢሕራም (ለሐጅ ወይም ዑምራ ኒያ) ካደረገች በኋላ የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ከታያት ከእርሱ እስክትጠራ ድረስ በካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ አይፈቀድላትም፡፡

19. ሴት ልጅ በአለባበስ ከወንዶች ጋር ከመመሳሰል፣ጌጦቿን ከመግለጥ እና (መገላለጥ) ከራቀች እና ከተጠነቀቀች ፈተና ላይ ከሚጥሉ ልብሶች ውጭ በፈለገችው ዓይነት ልብስ ኢሕራም ማድረግ ይፈቀድለታል፡፡

20. በሐጅና ዑምራ ኢሕራም(ኒያ) ወቅት (ለበይከ ሐጀን ወይም ለበይከ ዑምረተን ብሎ ከመናገር) ውጭ በሌሎች የአምልኮ አይነቶች ኒያንበልብ ከማሰብ ባሻገር (ለምሳሌ ነወይቱ አን-ኡሰሊ.... የመሳሰሉትን በማለት) በምላስ መናገር አዲስ ፈጠራ (ቢድዓ) ሲሆን በዚህ ላይ ድምፅን ከፍ ማድረጉ ደግሞ የከፋ ነው፡፡

21. ለአካለ መጠን የደረሰ አንድ ሙስሊምበጉዞውሐጅን ወይም ዑምራን ማድረግ የሚያስብ ከሆነ የኢሕራም ማድረጊያ ክልሎችን (ሚቃቶችን) ያለ ኢሕራም (ኒያ) ማለፉየተከለከለ ነው፡፡

22. ለሐጅ ወይም ዑምራ በአውሮፕላንየሚጓዝ ሰው በሚቃቱ ትይዩ በሚሆንበት ወቅት ኢሕራም (ኒያ) ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ከሚቃቱ ትይዩ ከመሆኑ በፊት ለኢሕራም መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በአውሮፕላን ውስጥ እንቅልፍ እንዳየወስደው ወይም እንዳይዘናጋ ስጋት ከገባው ከሚቃቱትይዩ ከመሆኑ በፊት ኢሕራም ቢያደርግ ችግር የለውም፡፡

23. ከሐጅ በኋላ ከተንዒም ወይም ከጁዕራናበመመላለስ አንዳንድ ሰዎች የሚፈፅሙት ዑምራን የማብዛት ሙከራ በሸሪዓየተደነገገ ስለመሆኑ ምንም አይነት መረጃ የለም፡፡

24. ሐጃጁ በእለተ አተርዊያ (ከዙልሂጃ ስምንተኛው ቀን) መካ ውስጥ ካለበት ቦታ ኢሕራም ያደርጋል ብዙዎች እንደሚያደርጉት መካ ውስጥወይም ከሚዛቡ(ካዕባ ላይ ያለው አሸንዳ) አጠገብ ነው ኢሕራም ማድረግ የግድ አይደለም፡፡ ከሚና በሚወጣበትም ጊዜ ምንም አይነት የተለየየመሰናበቻ ተግባር አይጠበቅበትም፡፡

25. በዘጠኛኛው ቀን ከሚና ወደ ዓረፋ የሚያደረገው ጉዞ ፀሐይ ከወጣች በኋላ መሆኑ የተመረጠ ነው፡፡

26. ከዓረፋ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት መንቀሳቀስ አይፈቀድም፡፡ ፀሐይ ከጠለቀችም በኋላ ሐጃጁ በእርጋታ እና ክብሩን በጠበቀ መልኩ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

27. በዚህ እለት የመግሪብ እና ኢሻዕ ሰላቶች የሚሰገዱት በመግሪብም ይሁን የኢሻዕ ወቅትሙዝደሊፋ ከደረሱ በኋላ ነው፡፡

28. ለጠጠር ውርወራ የሚሆኑ ጠጠሮችንከማንኛውም ቦታ መልቀም ይቻላል፤ (ስለሆነም)ጠጠሮችን ከሙዝደሊፋ መልቀም ግዴታ አይደለም፡፡

29. ለጠጠር ውርወራ የተለቀሙ ጠጠሮችን ማጠብ የተወደደ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ተግባር ከመልዕክተኛውም (ﷺ) ይሁን ከሰሐቦች የተገኘ አይደለም፡፡

30. ሴቶች፣ህፃናት እና የመሳሰሉ አቅመ ደካሞች በለሊቱ የመጨረሻ ክፍለ ግዜ ከሙዝደሊፋ ወደ ሚና እንዲንቀሳቀሱ ይፈቀድላቸዋል፡፡

31. ሐጃጁ በዒዱ ዕለት ሚና ደርሶ ጀምረተል-ዓቀባ ላይ ጠጠር መወርወር ሲጀምር ተልቢያን ያቋርጣል፡፡

32. በጠጠር ውርወራ ወቅት ግድ የሚሆነው ጠጠሩ እጉድጓዱ ውስጥ ማረፉ እንጂ (ነጥሮ ሳይወጣ) እዚያው መቅረቱ አይደለም፡፡

33. ይበልጥ ትክክለኛ በሆነው የዑለማዎች አቋም መሰረትየእርድ ማረጃው ወቅት እስከ አያመ-አታሽሪቅ መጨረሻ (ከዙልሒጃ ወር አስራ ሶስተኛ) ቀን ፀሐይ መጥለቂያ ድረስ ይቆያል፡፡

34. ጠዋፈል-ኢፋዳ ከሐጅማዕዘናት (ሩክኖች) መካከል አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም እርሱ ካልተፈፀመ ሐጅ ፈፅሞ የተሟላ

ሊሆን አይችልም፡፡ (ሆኖም) ሐጃጁ በሚና ከሚቆይባቸው ቀናት በኋላ ሊያቆየው ይችላል፡፡

35. ሐጅና ዑምራን አቆራኝቶ የሚፈፅም (ቃሪን) እንዲሁም ሐጅን ብቻ የሚፈፅም (ሙፍሪድ) ከአንድ ግዜ በላይሰዕይ ማድረግ የለባቸውም፡፡

36. ሐጃጁ የእርዱ (የዒዱ) እለት የሚፈፅማቸውን ተግባራት በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት ማድረጉ የተሻለ ነው፡ ፡

- ጀምረተል-ዓቀባ ላይ ጠጠር በመወርወር ይጀምራል፣ ከዚያም (ማረድ ግዴታ የሚሆንበት ከሆነ) እርዱን ያርዳል፣ ፀጉር መላጨቱን ወይም ማሳጠሩን ያስከትላል፣ ጠዋፍ በማድረግ ይቀጥል እና በመጨረሻም (ሰዕይ ማድረግ ካለበት) ሰዕይ በማደርግ ያጠናቅቃል፡፡ሆኖም አንዱን ከሌላኛው ቢስቀድምም ችግር የለውም፡፡

37. ሙሉ መፈታት (ማለትም ሰውየው በኢሕራም ምክንያት የተከለከላቸው ነገሮች ሁሉ የተፈቀዱ የሚሆኑበት ሁኔታ) ሊከሰትባቸው የሚችሉ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ.ጀምረተል-ዓቀባ ላይ ጠጠር መወርወር፡፡

ለ.ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር፡፡

ሐ.ጠዋፈል-ኢፋዳን (ሠዕይ ማድረግ ላለበት) ከሠዕይ ጋር ማከናወን፡፡

38. (በአስራ ሁለተኛው ቀን ጠጠር ከወረወረ በኋላ) ሐጃጁ ከሚና ለመውጣት ከተቻኮለ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ሚናን ለቆ መውጣት ግድ ይሆንበታል፡፡

39. ጠጠር መወርወር የማይችልሕፃን ሐላፊው የእራሱን ከወረወረ በኋላ ለእርሱ ይወረውርለታል፡፡

40. በበሽታ ወይም በእድሜ መግፋት አልያም በሌላ ምክንያት ጠጠር መወርወር የተሳነው ሰው በእርሱ ምትክ ጠጠር የሚወረውርለት ሰው መወከል ይችላል፡፡

41. ተወካዩ ከዕለቱ የጠጠር መወርወርያ ስፍራዎች በእያንዳንዳቸው በቅድሚያ ለእራሱ በመቀጠልም ለወከለው ሰው በድጋሚ መመለስ ሳያስፈልገው በአንድ ወቅት መወርወር ይችላል፡፡

42. ሐጃጁ ከመስጅደል ሀራም አቅራቢያ (ከመካ) ነዋሪዎች ካልሆነና (ሐጅ እና ዑምራ ስርአቱን) በሙተመቲዕነት ወይም ቃሪንነት ከፈፀመ ሀድይን ማቅረብየሚሆንበት ሲሆን እርሱም አንድ በግ ወይም ፍየል በነፍስወከፍ አልያም አንድ ግመል ወይም በሬ ለሰባት ነው፡፡

43. በተመቱዕ ወይም በቂራን (የሐጅና ዑምራ አፈፃፀም ሕግ መሰረት) ሐጅን እና ዑምራን የሚፈፅም ሰው ሐድይን ማረድ ከተሳነው ሶስት ቀን በሐጅ ላይ ሳለ እንዲሁም ሰባት ቀን ወደ ቤተሰቦቹ ሲመለስ መጾም ግዴታ ይሆንበታል፡፡

44. ሐጃጁ በዕለት ዓረፋ ጾመኛ ሆኖ እንዳይውል (የሚያርደው እርድ የሌለው በምሆኑ መጾም ካለበት) የሚጾማቸውን ሶስት ቀናት ከዚህ ቀን ማስቀደሙ የተሻለ ነው፡፡ ያንን ማድረግ ካልቻለም ሶስቱን የአያመ-አተሽሪቅ (ማለትም አስራ አንደኛውን፣አስራ ሁለተኛውን እና አስራ ሶስተኛውን) ቀናት ይፆማል፡፡

45. ሐጃጁ ከላይ የተጠቀሱትን የሶስት ቀናት ጾም አከታትሎም ይሁን አለያይቶ መጾም የሚፈቀድለት ቢሆንም ነገር ግን ከአያመ-አተሽሪቅ ማዘግየት የለበትም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም (ወደ አገሩ ሲመለስ የሚጾማቸውን) የሰባት ቀን ጾም በተመለከተ አከታትሎም ይሁን አለያይቶ መጾም ይፈቀድለታል፡፡

46. በወር አበባ እና በወሊድ ደም ላይ ካሉ ሴቶችውጭ በሌሎቹ ሐጃጆች ላይ ሁሉ የመሰናበቻ ጠዋፍን (ጠዋፈል-ወዳዕ) መድረግ ግዴታ ነው፡፡

47. የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጅድ ከሐጅ በፊትም ይሁን በኋላ አልያም ከአመቱ በማንኛውምወቅት መጎብኘት ሱና ነው፡፡

48. የነብዩን (ﷺ) መስጅድ (መስጅድ-አነበዊ) የሚጎበኝ ሰው (ማንኛውም መስጅድ ሲገባ የመጀመሪያው ተግባሩ ይህ እንደሆነው ሁሉ) ሁለት ረከዓን በመስጂዱ ማንኛውም ስፍራ በመስገድ መጀመሩ የተወደደ (ሱና) ሲሆን ሆኖም ሁለቱን ረከዓ በተከበረው ረውዳ ላይ መስገዱ የተሻለነው፡፡

49. የመዕክተኛውን (ﷺ) መካነ መቃብርንም ይሁን ሌሎችን መቃብሮች መጎብኘት ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ (የተደነገገ) ሲሆን ይህም (እርሱን ብቻ አስቦ) ስንቅ ሰንቆ መጓጓዣ አዘጋጅቶ መጓዝ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡

50. የተከበረው (የመልዕክተኛው (ﷺ) አካል ባረፈበት (የእናታችን አዒሻ)) ቤት ግድግዳ መተሻሸት ወይም እርሱን መሳም አልያም በርሱ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ ከቀደምት ደጋጎች (ከሰለፍ-አሳሊሀ) ያልተገኘ የተኮነነ

የፈጠራ (የቢድዓ) ተግባር ሲሆን በርሱ ዙሪያ ጠዋፍ በማድረግየታሰበው ወደ መልዕክተኛው (ﷺ) (በአምልኮ) መቃረብ ከሆነ ደግሞ (ከኢስላም የሚስወጣ) ትልቁ ሽርክ ይሆናል፡፡

51. ማነኛውም ሰው መልዕክተኛውን (ﷺ) ጉዳዩን እንዲፈፅሙለት፣ከጭንቅ እንዲገላግሉት ሊጠይቅ አይፈቅድለትም፤ ምክንያቱም ይህ የሽርክ ተግባር ነውና፡፡

52. የመልዕክተኛው (ﷺ) የቀብር ውስጥ ሕይወት ከመሞታቸው በፊት እንደነበረው አይነት ሳይሆን ምንነቱን እና ሁኔታውን አላህ (ﷻ) እንጂ ማንም የማያውቀው በዚህኛው እና በወዲያኛው ዓለም መካከል ጋርዶ የሚገኘው (የበርዘኽ)ዓለም ሕይወት ነው፡፡

53. አንዳንድ (የመልዕክተኛውን (ﷺ) መስጅድ የሚጎበኙ) ጎብኚዎች ሆን ብለው ዱዓቸውንየመልዕክተኛው (ﷺ) ቀብር አጠገብ ለማድርግመጠባበቃቸው፣ወደ ቀብሩም ዞረው (ለዱዓእ) እጆቻቸውን ማንሳታቸው መሰረት የሌለው የፈጠራ (የቢድዓ) ተግባር ነው፡፡

54. አንዳንድ (ለእውቀት ቅርበት የሌላቸው) ሰዎች እንደሚገምቱት የመልዕክተኛውን ቀብር መጎብኘት ለሐጅ ግዴታም ይሁን መስፈርት አይደለም፡፡

55. ወደ መልዕክተኛው( ﷺ) ቀብር ስንቅን ሰንቆ መጓዝበሸሪዓ መሰረት ያለው እና የተደነገገ ነው ሲሉ አንዳንድ ሰዎች በማስረጃነት የሚጠቅሷቸው ሀዲሶች ባጠቃላይ ከሰነድ አንፃር (መርጃ ሆነው መቅረብ

የማይችሉ)ደካሞች (ደኢፍ) አልያም የተቀጠፉ (መውዱዕ) ሀዲሶች ናቸው::

# በዓረፋ፣ በመሽዐረል ሀራም እና በሌሎችም ቦታዎች ሊደረጉ የሚችሉ ዱዐዎች

በዓረፋ በመሽዓረል-ሀራም (ሙዝደሊፋ) እና ከዚያም ውጭ ባሉ ዱዓእ የበለጠ ተቀባይነት በሚያገኝባቸው ቦታዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዱዓዎች ወይም በተወሰኑት ዱዓእ ማድረጉ የተመረጠ ነው::

اللَّهمَّ إنِ أَسألُكَ العَفو والعَافِيَةَ في دِيني ودُنيايَ، وأهلي ومَالي، اللَّهمَّ استُر عَوْرَاتِي، وآمِنْ رَوْعَاتِي، اللَّهمَّ احفظني من بَينِ يَدَيَّ ومِن خَلْفي، وَعن يَميني، وعن شِمالي ، ومِن فَوقي، وأعُوذُ بِعَظَمَتِكَ أنْ أُغْتَالَ مِنْ تَحتِي.

1. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አልዓፍወ ወልዓፊየተ ፊዲኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ አላሁመ እስቱር ዐውራቲ ወአሚን ረውዓቲ አላሁመ እህፊዝኒ ሚን በይኒ የደየ ወሚን ኽልፊ ወዓን የሚኒ ወዓን ሺማሊ ወሚን ፊውቂ ወአዑዙ ቢዓዘመቲከ አንኡግታለ ሚንታህቲ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! በዲኔ፣ በዱንያዊ ህይወቴ፣ በቤተሰቤና በንብረቴ ደህንነትን እንድትሰጠኝ፣ ምህረትን እንድታደርግልኝ እጠይቅሀለሁ:: አላህ ሆይ! ገመናዬን ሸፍንልኝ፣ ስጋቴን አስወግድልኝ:: አላህ ሆይ! ከፊት ለፊቴ፣ ከኋላዬ፣ ከቀኜ፣ ከግራዬ፣ ከበላዬ ጠብቀኝ::

ከበታቼም በድንገት ከሚመጣ አደጋ እና ጥቃት በልቅናህ እጠበቃለሁ::

اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي بَدَنِي، اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي سَمْعِي، اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي بَصَرِي، لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ. اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ الْكُفْرِ وَالْفَقْرِ ومِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ. اللَّهُمَّ أَنتَ رَبي لا إلهَ إلا أنتَ، خَلَقْتَني وَأَنَا عبدُك ، وَأَنَا على عَهْدِكَ ووَعدِكَ مَا اسْتَطَعتُ ، أَعُوذُ بِكَ مِن شَرِّ ما صَنَعتُ ، أَبُوءُ لَكَ بنعْمَتكَ عَليَّ ، وَأَبُوءُ بِذَنْبِي، فاغْفِرلِي، إنه لا يغفرُ الذنوبَ إلا أنتَ. اللَّهُمَّ إِنِّى أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْهَمِّ وَالْحَزَنِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ الْعَجْزِ وَالْكَسَلِ، وَمِنَ الْبُخْلِ وَالْجُبْنِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ غَلَبَةِ الدَّيْنِ، وَقَهْرِ الرِّجَالِ. اللهم اجعل أول هذا اليوم صلاحًا وأوسطه فلاحًا، وآخره نجاحًا، وأسألك خيري الدنيا والآخرة يا أرحم الراحمين.

2. **"አላሁመ ዓፊኒ ፊበደኒ አላሁመ ዓፊኒ ፊሰምዒ፣ አላሁመ ዓፊኒ ፊበሰሪ፣ ላኢላሃ ኢላ አንተ፣ አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚነልኩፍሪ ወልፈቅሪ ወሚን ዐዛቢልቀብሪ፣ ላኢላሃ ኢላ አንተ""አላሁም አንተ ረቢ ላኢላሃ ኢላ አንተ ኸለቅተኒ ወዓነ ዐብዱከ ወዓነ ዓላ ዓህዲከ ወወዕዲከ መስተጣዕቱ አዑዙቢከ ሚን ሸሪ ማሰነዕቱ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዓለየ ወአቡኡ ቢዘንቢ ፈግፊርሊ ኢነሁ ላየግፊሩ አዙኑበ ኢላ አንተ""አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልሀሚ ወልሀዝኒ ወአዑዙቢከ ሚነልዐጅዚ ወልከሰሊ ወሚነልቡኽሊ ወልጁብኒ ወአዑዙቢከ ሚንገለበቲ አደይኒ ወቀህሪ አሪጃል አላሁመ እጅዓል አወለ ሀዘልየውም ሰላሀን ወአውሰጠሁ ፈላሀን**

ወአኺረሁ ነጃሀን ወአስአሉከ ኸይረይ አዱንያ ወልአኺራ ያአርሀመ አራሂሚን”

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! መላ አካሌን ጤናማ አድርግልኝ። አላህ ሆይ ! መስሚያዬን ጤናማ አድርግልኝ። አላህ ሆይ! መመልከቺያዬን ጤናማ አድርግልኝ። ከአንተ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም። አላህ ሆይ! ከክህደት፣ ከድህነትና ከቀብር ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ። ከአንተ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም።አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ፤ ከአንተም ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም። ፈጥረኸኛል፤ እኔ ባሪያህ ነኝ፤ እኔም የቻልኩትን ያክል ቃል ኪዳኔን ለመሙላት በመጣር ላይ ነኝ። ከሰራሁት ወንጀል ክፉት በአንተ እጠበቃለሁ። በኔ ላይ የዋልከውን ውለታ አምናልሁ፤ ወንጀልኛ መሆኔንም አምናለሁ፤ እነሆ! ከአንተ ሌላ ወንጀልን የሚምር የለምና ማረኝ። አላህ ሆይ! ከጭንቀትና ትካዜ በአንተ እጠበቃለሁ፤ ከደካማነትና ከስልቹነት፤ ከስስትና ፍርሃት በአንተ እጠበቃለሁ። ከእዳ ጫናና ከሸንፈትም በአንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! የዚህን እለት መጀመሪያ መስተካከያ መሀከለኛውን ነፃ መውጫ መጨረሻውን ድል መጎናጸፍያ አድርገው። አንተ የአዛኞች ሁሉ አዛኝ (አላህ) ሆይ! በቅርቢቱም ይሁን በወዲያኛው ዓለም መልካሙን እለምንሃለሁ።

اللَّهمَّ إني أَسأُلكَ الرِّضىَ بعدَ القَضاءِ ، وبَردَ العَيشِ بَعدَ المَوتِ، وَلَذَّةَ النظر إلى وَجهِكَ الكريمِ، والشَّوقَ إلى لِقَائِكَ، في غير ضَرَّاءَ مُضِرَّةٍ ، ولا فِتْنَةٍ مُضِلَّة، وأَعُوذُ بِكَ أَنْ أَظْلِمَ أَوْ أُظْلَمَ، أَوْ أَعْتَدِيَ أَوْ يُعْتَدَى عَلَيَّ، أَوْ أَكْتَسِبَ خَطِيئَةً أَوْ ذَنْبًا لَا تغْفرُه.

3. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አሪዳ በዕደልቀዷኢ ወበርደልዐይሺ በዕደልመውቲ ወለዘተ አነዘሪ ኢላወጅሂከልከሪም ወሸወቀ ኢላ ሊቃኢከ ፊገይሪ ደራአ ሙዲረቲን ወላፊትነቲን ሙዲላ ወአዑዙቢከ አንአዝሊመ አውኡዝለመ አውአዕተዲየ አውዩዕተዳ ዐለየ አውአክተሲበ ኸጢአተን አውዘንበን ላተግፊርሁ”**

**ትርጉሙም፡-** አላህ ሆይ! ከፍርድህ በኋላ ውሳኔን በፀጋ መቀበልን፣ ከሞት በኋላ ሰላማዊ ህይወትን፣ ክቡር ፊትህን በማየት የሚገኝ እርካታን፣ ከባድ ጉዳትና አጥማሚ ፈተና ወደ እኔ ከመምጣቱ በፊት ካንተ ጋር የመገናኘትን ናፍቆት እንድትለግሰኝ እለምንሃልሁ:: አላህ ሆይ! ከመበደል ወይም በሌሎች ከመበደል፣ ድንበር ከማለፍ ወይም በሌሎች ድንበር እንዳይታለፍብኝ፣ አልያም ኀጢአትን ከመስራት ወይም አንተ የማትምረውን ወንጀል ከመፈፀም በአንተ እጠበቃለሁ::

اللَّهمَّ إِني أَعُوذُ بِكَ أَنْ أُرَدَّ إِلَى أَرْذَلِ الْعُمُرِ. اللَّهُمَّ اهدِنِي لأحسَنِ الأعمالِ والأخلاقِ لا يَهْدِي لأَحسَنِها إِلا أَنتَ. واصرف عني سيئها لا يصرف عني سيئها إلا أنت.

4. **“አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚን አን ኡረደ ኢላ አርዘሊልዑሙሪ አላሁመ ኢህዲኒ ሊአህሰኒል አዕማል ወልአኽላቅ ላየህዲ ሊአህሰኒሃ ኢላ አንተ ወስሪፍዐኒ ሰይአሃ ላየስሪፉ ዐኒ ሰይአሃ ኢላ አንተ”**

**ትርጉሙም፡-** አላህ ሆይ! ከመጃጀት በአንተ እጠበቃለሁ:: አላህ ሆይ! ወደ በጎ ስራና ወደ መልካም ሥነ-ምግባር ካንተ ሌላ የሚመራ የለምና ለበጎ ስራና ለመልካም ሥነ-

ምግባር ምራኝ:: ካንተም ሌላ ከኔ ክፉ ስራንና መጥፎ ባህሪን የሚያርቅ የለምና አርቅልኝ::

اللهم أصلح لي ديني، ووسع لي في داري، وبارك لي في رزقي.

اللهم إني أعوذ بك من القسوة والغفلة والذلة والمسكنة،

وأعوذ بك من الكفر والفسوق والشقاق والسمعة والرياء.

وأعوذ بك من الصمم والبكم والجذام وسيء الأسقام.

5. **"አላሁመ አስሊህሊ ዲኒ ወወሢዕሊ ፊዳሪ ወባሪክሊ ፊሪዝቂ አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚነልቀስዋ ወልገፍላ ወዙላ ወልመስከና ወአዑዙቢከ ሚነልኩፍሪ ወልፉሱቂ ወሺቃቂ ወሱምዓቲ ወሪያኢ ወአዑዙቢከ ሚነአስመሚ ወልበክሚ ወልጁዛሚ ወሰዬኢል አስቃሚ"**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! እምነቴን አስተካክልልኝ፤ ቤቴን አስፋልኝ፤ ሲሳዬን ባርክልኝ:: አላህ ሆይ! ከልብ ድርቀት፣ አንተን ከመዘናጋት፣ ከውርደትና ከድህነት በአንተ እጠበቃለሁ:: ከክህደት፣ ከአመፅ፣ ከጨቅጫቃነት፣ ከይስሙልኝና ይዩልኝ በአንተ እጠበቃልሁ:: ከደንቆሮነት፣ ከዱዳነት፣ ከቁምጥናና ከማነኛውም ክፉ በሽታም በአንተ እጠበቃለሁ::

اللَّهمَّ آتِ نَفسي تَقْوَاها ، وزَكِّها أَنت خَيرُ مَنْ زكَّاهَا ، أَنتَ وَلِيُّها ومولاها، اللَّهمَّ إِني أَعوذ بك من علم لا ينفعُ ، وقَلبٍ لا يَخشَع ، ونَفسٍ لا تشبع ، ودعوة لا يُستَجَاب لها.

6. **"አላሁመ አቲ ነፍሲ ተቅዋሃ ወዘኪሃ አንተ ኸይሩ መንዘካሃ አንተ ወሊዩሃ ወመውላሃ አላሁመ ኢኒ**

**አዑዙቢከ ሚን ዒልሚን ላየንፈዑ ወቀልቢን ላየኽሸዑ ወነፍሲን ላተሽበዑ ወዳዕወቲን ላዩስተጃቡ ለሃ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ለነፍሴ አንተን መፍራትን (ተቅዋን) ለግሳት፡፡ አጥራትም ከአንተ ሌላ የሚያጠራት የለምና፡፡ አንተ ጌታዋም ረዳቷም ነህ፡፡ አላህ ሆይ! ከማይጠቅም ዕውቀት፣ ፈጣሪውን ከማይፈራ ልብ፣ ከማትጠግብ ነፍስ፣ ተቀባይነት ከማያገኝ ዱዓም በአንተ እጠበቃለሁ፡፡

اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا عَمِلْتُ، وَمِنْ شَرِّ مَا لَمْ أَعْمَلْ، وأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا عَلِمْتُ، وَمِنْ شَرِّ مَا لَمْ أَعلم. اللَّهمَّ إِنِي أعوذ بك من زوال نِعْمَتِكَ ، وتَحَوُّلِ عافِيَتك ، وفُجاءةِ نقمَتك ، وجميع سخطِك.

7. **“አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚንሸሪ ማዐሚልቱ ወሚንሸሪ ማለም አዕመል ወአዑዙቢከ ሚንሸሪ ማዓሊምቱ ወሚንሸሪ ማለም አዕለም አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚንዘዋሊ ኒዕመቲከ ወተሀዉሊ ዓፌየቲከ ወፉጀአቲ ኒቅመቲከ ወጀሚዒ ሠኸጢከ”**

   **ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ከሰራሁት ክፉ ስራ ውጤትና ምናልባት ወደ ፊት ልሰራው ከምችለው ክፉ ስራ ውጤት በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ ካወቅኩትና ካላወቅኩትም ክፉ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ከጸጋህ መወገድ፣ ከለገስከኝ ሰላምና ጤንነት መለወጥ፣ ከድንገተኛ ብቀላህና ከቁጣህም ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡

اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْهَدْمِ وَالتَّرَدِّي ، وَمِنَ الْغَرَقِ وَالْحَرقِ وَالْهَرَمِ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ أَنْ يَتَخَبَّطَنِي الشَّيْطَانُ عِنْدَ الْمَوْتِ ، وَأَعُوذُ بِكَ أَنْ أَمُوتَ لَدِيغًا، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ طَمَعٍ يَهْدِي إِلَى طَبْعٍ.

8. **"አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚንልሀድሚ ወተረዲ ወሚነል ገረቂ ወልሐርቂ ወልሀረሚ ወአዑዙብከ ሚን አየተኸበጠኒ አሸይጣኑ ዒንደልመውቲ ወአዑዙቢከ ሚን አንአሙተ ለዲገን ወአዑዙቢከ ሚን ጠመዒን የህዲ ኢላጠብዒን"**

   **ትርጉሙ፦** አላህ ሆይ! አንድ ነገር ፈርሶ ከሚያስከትለው ጥፋት፣ ከፍ ካለ ቦታ በመውደቅ፣ (ውሃ ውስጥ) በመስጠም፣ በቃጠሎ ከሚደርሱ አደጋዎች እንዲሁም ከመጃጀት በአንተ እጠበቃለሁ:: በመሞቻ ጊዜዬ በሸይጣን ከመሸንገል በአንተ እጠበቃለሁ:: ተነድፌ ከመሞት በአንተ እጠበቃለሁ:: ጠባዬ ሆኖ ከሚቀር ስግብግብነትም በአንተ እጠበቃለሁ::

اللهمَّ إنِي أعوذُ بكَ منْ مُنكراتِ الأخلاقِ والأعمالِ والأهواءِ والادواءِ ، وأعوذ بك من غَلَبَةِ الدَّيْنِ، وقَهرِ الرجال، وَشَمَاتَةِ الْأَعْدَاءِ.

9. **"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሙንከራቲል አኽላቂ ወልአዕማል ወልአህዋእ ወልአድዋኢ ወአዑዙቢከ ሚን ገለበቲ አደይኒ ወቀህሪ አሪጃል ወሽማተቲል አዕዳእ"**

   **ትርጉሙ፦** አላህ ሆይ! ከመጥፎ ስነ-ምግባር፣ ከክፉ ስራ፣ ስሜትን ከመከተል እና ከበሽታ በአንተ እጠበቃለሁ:: ከእዳ ጫና ከጭቆናና የጠላት መሳቂያ ከመሆንም በአንተ እጠበቃለሁ::

اللَّهُمَّ أَصْلِحْ لِى دِينِىَ الَّذِى هُوَ عِصْمَةُ أَمْرِى، وَأَصْلِحْ لِى دُنْيَاىَ الَّتِى فِيهَا مَعَاشِى، وَأَصْلِحْ لِى آخِرَتِى الَّتِى فِيهَا مَعَادِى، وَاجْعَلِ الْحَيَاةَ زِيَادَةً لِى فِى كُلِّ خَيْرٍ، وَاجْعَلِ الْمَوْتَ رَاحَةً لِى مِنْ كُلِّ شَرٍّ ، رَبِّ أَعِنِّي ولا تُعِنْ عَلَيَّ ، وانْصُرْنِي ولا تَنْصُرْ عَلَيَّ ، واهدِنِي ويَسِّرْ الْهُدَى لِي.

10. "አላሁመ አስሊሕሊ ዲኒየለዚ ሁወ ዒስመቱ አምሪ ወአስሊሕሊ ዱንያየለቲ ፊሃ መዓሺ ወአስሊህሊ አኺረቲለቲ ፊሃ መዓዲ ወጅዐሊልሃያተ ዚያደተንሊ ፊኩሊ ኸይሪን ወጅዐሊልመውተ ራሐተንሊ ሚንኩሊ ሸሪን ረቢ አዒኒ ወላቱዒን ዐለየ ወንሱርኒ ወላተንሱር ዐለየ ወህዲኒ ወየሲር አልሁዳ ሊ"

ትርጉሙም፦ አላህ ሆይ! የነገሬ ሁሉ ማስተካከያ የሆነውን ዲኔን አስተካክልልኝ:: ጊዜያዊ መኖሪያዬ የሆነችውን ዱንያዬን አብጅልኝ መመለሻዬ የሆነውንም የመጪውን ዓለም አስተካክልልኝ:: የህይወት ዘመኔን መልካም ነገሮችን የማበዛበት አድርግልኝ:: ሞቴን ደግሞ ከክፉ ነገሮች የምገላገልበት አድርገው:: ጌታዬ ሆይ! አግዘኝ በኔ ላይ (ጠላቴን) አታግዝ:: እርዳኝ በኔ ላይ (ጠላቴን) አትርዳ:: ቅኑን መንገድ ምራኝ እርሱንም አግራልኝ::

اللَّهُمَّ اجْعَلْنِى ذَكَّارًا لَكَ، شَكَّارًا لَكَ، مِطْوَاعًا لَكَ، مُخْبِتًا إِلَيْكَ، أَوَّاهًا مُنِيبًا، رَبِّ تَقَبَّلْ تَوْبَتِي، وَاغْسِلْ حَوْبَتِي، وَأَجِبْ دَعْوَتِي، وَثَبِّتْ حُجَّتِي، وَاهْدِ قَلْبِي، وَسَدِّدْ لِسَانِي، وَاسْلُلْ سَخِيمَةَ صَدْرِي.

11. "አላሁመ እጅዓልኒ ዘካረን ለከ ሸካረን ለከ ሚጥዋዐን ለከ ሙኽቢተን ኢለይከ አዋሃን ሙኒባ ረቢ ተቀበል ተውበቲ

**ወግሲል ሀውበቲ ወአጂብ ደዕወቲ ወሰቢት ሁጃቲ ወህዲ ቀልቢ ወሰዲድ ሊሳኒ ወስሉል ሰኺመቲ ሰድሪ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! አብዝቶ አንተን የሚያስታውስ፣ የሚያመሰግን፣ ዘውትር ላንተ ታዛዥ፣ የሚዋረድ፣ አልቃሻና ወደ አንተ ተመላሽ አድርገኝ:: ጌታዬ ሆይ! ንሰሃዬን ተቀበለኝ ወንጀሌን እጠብልኝ:: ልመናዬን ተቀበለኝ ማስረጃዬን አፅናልኝ:: ልቦናዬን አቅናልኝ:: አንደበቴን የተስተካከለ አድርግልኝ:: በልቤ ወስጥ ያለውንም መጥፎ ፍላጎት ሁሉ አውጣልኝ::

اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الثَّبَاتَ فِي الْأَمْرِ ، وَالْعَزِيمَةَ عَلَى الرُّشْدِ ، وَأَسْأَلُكَ شُكْرَ نِعْمَتِكَ وَحُسْنَ عِبَادَتِكَ ، وَأَسْأَلُكَ قَلْبًا سَلِيمًا ، وَلِسَانًا صَادِقًا ، وَأَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِ مَا تَعْلَمُ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا تَعْلَمُ ، وَأَسْتَغْفِرُكَ مِمَا تَعْلَمُ ، وَأَنْتَ عَلَّامُ الْغُيُوبِ.

12. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አሰባተ ፊልአምር ወልዓዚመተ ዓለሩሽድ ወአስአሉከ ሹክረ ኒዓመቲከ ወሂስኒ ዒባደቲክ ወአስአሉከ ቀልበን ሰሊመን ወሊሳነን ሳዲቀን ወአስአሉከ ሚን ኸይሪ ማተዕለሙ ወአዑዙ ቢከ ሚንሸሪ ማተዕለሙ ወአስተግፊሩከ ሚማ ተዕለሙ ወአንተ ዓላሙልጉዩብ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! በጉዳዬ ላይ ፅናትን በቀናው መንገድ ላይ ቆራጥነትን እጠይቅሃለሁ:: ፀጋህን እንዳመሰግን አምልኮህን እንዳሳምር እንድትረዳኝ እለምንሃለሁ:: ንፁህ ልቦናን እውነተኛ አንደበትን እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ::አንተ የምታውቀውን መልካም ነገር ሁሉ እንድትሰጠኝ እማፀንሃልሁ:: ከምታውቀው ክፉ ነገር ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ:: እኔ ከማላውቀው አንተ

ከምታውቀው ወንጀሌም ሁሉ ምህረትንህን እለምናለሁ። አንተ የሩቁን ሁሉ አዋቂ ነህና።

اللَّهُمَّ أَلْهِمْنِي رُشْدِي وَقِنِي شَر نَفْسِي. اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ فِعْلَ الْخَيْرَاتِ وَتَرْكَ الْمُنْكَرَاتِ ، وَحُبَّ الْمَسَاكِينِ ، وَأَنْ تَغْفِرَ لِي وَتَرْحَمَنِي ، وَإِذَا أَرَدْتَ بِعِبَادِكَ فِتْنَةً ، فَتَوَفَّنِي إِلَيْكَ غَيْرَ مَفْتُونٍ.

13. **“ አላሁመ አልሂምኒ ሩሽዲ ወቂኒ ሸረ ነፍሲ አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ፊዕለል ኸይራት ወተርከል ሙንከራት ወሁበል መሳኪን ወአን ተግፊረ ሊ ወተርሃምኒ ወኢዛ አርድተ ቢዒባዲከ ፊትነተን ፈተወፈኒ ኢለይከ ገይረ መፍቱን”**

    **ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ቀናውን መንገድ አሳውቀኝ። ከነፍሴም ክፋት ጠብቀኝ። አላህ ሆይ! መልካም ሥራዎችን እንድሰራ፣ መጥፎ ሥራዎችን እንድርቅና ድሆችን እንድወድ እንድታደርገኝ፤ እንድትምረኝና እንድታዝንልኝም እለምንሃለሁ። በባሮችህ ላይ ፈተናን በፈለግክ ግዜም ሳልፈተን እንድትወስደኝ እማፀንሃለሁ።

اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ حُبَّكَ وَحُبَّ مَنْ يُحِبُّكَ ، وَحُبَّ كل عَمَلٍ يُقَرِّبُنِي إِلَى حُبِّكَ. اللَّهُمَّ إِنِي أَسْأَلُكَ خَيْرَ الْمَسْأَلَةِ ، وَخَيْرَ الدُّعَاءِ وَخَيْرَ النَّجَاحِ ، وَخَيْرَ الثَّوَابِ ، وَثَبِّتْنِي وَثَقِّلْ مَوَازِينِي ، وححق إِيمَانِي ، وَارْفَعْ دَرَجَتِي ، وَتَقَبَّلْ صَلاتِي وعبادتِي ، وَاغْفِرْ خَطِيئَاتِي ، وَأَسْأَلُكَ الدَّرَجَاتِ الْعُلَى مِنَ الْجَنَّةِ .

14. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሁበከ ወሁበ መን ዩሂቡከ ወሁበ ኩለ ዓመሊን ዩቀሪቡኒ ኢላ ሁቢከ አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ**

**ኸይረል መስአላ ወኸይረዱዓእ ወኸይረነጃህ ወኸይረል ዓመል ወኸይረ ሰዋብ ወሰቢትኒ ወሰቂል መዋዚኒ ወሃቂቅ ኢማኒ ወርፈዕ ደረጃቲ ወተቀበል ሰላቲ ወግፈር ኸጢአቲ ወአስአሉከ ደረጃተል ዑላ ሚነል ጀና”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! አንተን መውደድን፣ አንተን የሚወዱ አካላትን መውደድን፣ ወደ አንተ የሚያቀርቡ ስራዎችን መውደድን እንድትሰጠኝ እማፀንሃለሁ። አላህ ሆይ! መልካም ልመናን፣ መልካም ዱዓን፣ መልካም ውጤትንና የተሻለ ምንዳን እንድትሰጠኝ እጠይቀሃለሁ። ፅናትን ስጠኝ፤ የመልካም ሥራ ሚዛኔን የሚያመዝን አድርግልኝ፤ ኢማኔን አረጋግጥልኝ፤ ደረጃዬን ከፍ አድርግልኝ፤ ሰላቴን፣ በአጠቃላይ አምልኮቴን ተቀበለኝ፤ ወንጀሌን ማርልኝ፤ ከጀነትም ከፍተኛውን ደረጃ እንድትሰጠኝ እማፀንሃለሁ።

اللَّهُمَّ إِنِي أَسْأَلُكَ فَوَاتِحَ الْخَيْرِ وَخَوَاتِمَهُ وَجَوَامِعَهُ ، وَأَوَّلَهُ وَآخِرَهُ ، وَظَاهِرَهُ وَبَاطِنَهُ ، وَالدَّرَجَاتِ الْعُلَى مِنَ الْجَنَّةِ.

15. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ፈዋቲሃል ኸይሪ ወኸዋቲመሁ ወጀዋሚዓሁ ወአወለሁ ወአኺረሁ ወዛሂረሁ ወባጢነሁ ወደረጃቲል ዑላ ሚነልጀና”**

    **ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! የመልካምን ነገር መክፍቻውን፣ ማሳረጊያውን፣ መልካሙን ሁሉ ያጠቃለለውን፣ መጀመሪያውንና መጨረሻውን፣ ግልጹንም ስውሩንም እጠይቅሃለሁ። ከጀነትም ከፍተኛውን ደረጃ እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ።

اللهم إني أسألك أن ترفع ذكري، وتضع وزري، وتطهر قلبي، وتحصن فرجي، وتغفر لي ذنبي.

16. **"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አንተርፈዐ ዚክሪ ወተደዐ ዊዝሪ ወቱጠሂረ ቀልቢ ወቱሀሲነ ፈርጂ ወተግፊረሊ ዘንቢ"**

   **ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! በመልካም ስታወስ የምኖር እንድታደርገኝ፣ የኀጢአቴ ሸክሜን እንድታወርድልኝ፣ ልቤን እንድታጠራልኝ፣ ሀፍረቴን (ከሀራም) እንድትጠብቅልኝና ወንጀሌን እንድትምረኝ እለምንሃለሁ።

اللهم إني أسألك أن تبارك في سمعي، وبصري، وفي روحي، وفي خَلقي، وفي خُلقي، وفي أهلي وفي محياي، وفي عملي، وتقبل حسناتي، وأسألك الدرجات العلى من الجنة.

17. **"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አንቱባሪከ ፊሰምዒ ወፊበሰሪ ወፊኸልቂ ወፊኹሉቂ ወፊአህሊ ወፊመሕያየ ወፊዓመሊ ወተቀበል ሃሰናቲ ወአስአሉከ አደረጃቲል ዑላ ሚነልጀና"**

   **ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! መስሚያዬን፣ መመልከቻዬን፣ አፈጣጠሬን፣ አጠቃላይ ስነ-ምግባሬን፣ ቤተሰቤን፣ ህይወቴን፣ ስራዬን እንድትባርክልኝና በጎ ስራዬን እንድትቀበለኝ እማፀንሃለሁ። ከጀነትም ከፍተኛውን ደረጃ እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ።

اللهم إني أعوذ بك من جهد البلاء ودرك الشقاء، وسوء القضاء، وشماتة الأعداء، اللهم مقلب القلوب، ثبت قلبي على دينك. اللهم مصرف القلوب والأبصار، صرف قلوبنا على طاعتك.

18. **“አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ጀህዲል በላኢ ወደረኪ አሽቃኢ ወሱኢልቀዳኢ ወሸማተቲል አዕዳኢ አላሁመ ሙቀሊበልቁሉቢ ሰቢት ቀልቢ ዓላ ዲኒክ አላሁመ ሙሰሪፈል ቁሉቢ ሰሪፍ ቁሉበና ዓላ ጣዓቲክ”**

**ትርጉሙም፦** ኣላህ ሆይ! ከአስጨናቂ ችግር፣ ከጥፋት፣ ከመጥፎ ውሳኔ፣ የጠላት መደሰቻ ከመሆን በአንተ እጠበቃለሁ:: አላህ ሆይ! ልቦችን ገለባባጭ የሆንክ ልቤን በዲንህ ላይ አፅናው:: አላህ ሆይ! አንተ ልብን የምትለዋውጥ የሆንክ ልቤን አንተን መታዘዝ ላይ አድርጋት::

اللهم زدنا ولا تنقصنا وأكرمنا ولا تهنا، وأعطنا ولا تحرمنا، وآثرنا ولا تؤثر علينا. اللهم أحسن عاقبتنا في الأمور كلها، وأجرنا من خزي الدنيا وعذاب الآخرة.

19. **“አላሁመ ዚድና ወላ ተንቁስና ወአክሪምና ወላቱሂና ወአዕጢና ወላ ተህሪምና ወኣሲርና ወላ ቱእሲር ዓለይና አሏሁመ አህሲን ዓቂበተና ፊልኡሙሪ ኩሊሃ ወአጂርና ሚን ሂዝዪ አዱንያ ወዓዛቢል አኺራ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ከመልካሙ ጨምርልን አታጉድልብን፤ አክብረን አታዋርደን፣ ለግሰን አትንፈገን፣ አብልጠን በኛ ላይ አታስበልጥ፣ አላህ ሆይ በማንኛውም ነገር ላይ ሁሉ ፍጻሚያችንን አብጅልን ከዚህ ዓለም ውርደት ከመጪውም ዓለም ቅጣት ሰውረን::

اللهم اقسم لنا من خشيتك ما تحول به بيننا وبين معصيتك، ومن طاعتك ما تبلغنا به جنتك، ومن اليقين ما تهون به علينا مصائب الدنيا، ومتعنا

بأسماعنا وأبصارنا وقواتنا ما أحييتنا واجعلها الوارث منا، واجعل ثأرنا على من ظلمنا، وانصرنا على من عادانا، ولا تجعل الدنيا أكبر همنا ولا مبلغ علمنا ولا تجعل مصيبتنا في ديننا ولا تسلط علينا بذنوبنا من لا يخافك ولا يرحمنا.

20. **"አላሁመ እቅሲም ለና ሚንኸሽየቲከ ማተሁሉ ቢሂ በይነና ወበይነ መዕሲየቲክ ወሚን ጣዓቲከ ማቱበሊጉና ቢሂ ጀነተከ ወሚነል የቂኒ ማቱሃዊሉ ቢሂ ዓለይና መሳኢበ አዱንያ ወመቲዕና ቢአስማዒና ወአብሳሪና ወቁዋቲና ማአህየይተና ወጅዓልሁል ዋሪሰ ሚና ወጅዓል ሰዕረና ዓላመን ዘለመና ወንሱርና ዓላ መን ዓዳና ወላተጅዓሊዱንያ አክበረ ሀሚና ወላ መብለገ ዒልሚና ወላ ተጅዓል ሙሲበተና ፊ ዲኒና ወላ ቱሰሊጥ ዓለይና ቢዙኑቢና መንላየኻፉከ ወላየርሃሙና"**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! በኛና በወንጀል መካከል ሊጋርድ የሚችልን የአንተን ፍራቻ፣ ከበጎ ተግባር ወደ ጀነት የሚያደርሰንን፣ በዱንያ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚያቀልልንን ከአንተ ጋር የመገናኘት እርግጠኝነትን(የቂንን) ስጠን፡፡ በጆሮዎቻችን፣ በዓይኖቻችንና በሀይላችን በህይወት እስካለን ተጠቃሚነትን ለግሰ፤ እስከ እለተ ሞታችንም አቆይልን፡፡ የበደሉንን ተበቀልልን፤ በጠላቶቻችንም ላይ የበላይነትን ስጠን፡፡ ዱንያን ትልቅ ጭንቀታችንና የእውቀታችን ማብቂያ አታድርጋት፡፡ በዚህች ዓለም የሚደርስብንን ችግር በዲናችን ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር አታድርግብን፡፡ በወንጀላችንም ምክንያት አንተን የማይፈራን ለኛ የማያዝንን እንዳትሾምብን፡፡

اللهم إني أسألك موجبات رحمتك، وعزائم مغفرتك، والغنيمة من كل بر، والسلامة من كل شر، والفوز بالجنة، والنجاة من النار.

21. **“አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሙጂባቲ ራህመቲክ ወዓዛኢመ መግፊረቲክ ወልገኒመተ ሚንኩሊ ቢርን ወሰላመተ ሚንኩሊ ኢስሚን ወልፊውዘ ቢልጀነቲ ወነጃተ ሚነናር”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! የአንተን ሀዘኔታ የሚያስገኙልኝን ነገሮች ሁሉ፣ ምህረትህን የሚያሰጡኝን፣ ከበጎ ስራዎች ሁሉ ማትረፍን፣ ከኀጢአት ሁሉ መራቅን ጀነትን መታደልንና ከእሳት ነጻ መሆንን እንድትለግሰኝ እለምንሃለሁ::

اللهم لا تدع لنا ذنباً إلا غفرته، ولا عيباً إلا سترته، ولا هماً إلا فرجته، ولا ديناً إلا قضيته، ولا حاجة من حوائج الدنيا والآخرة هي لك رضاً ولنا فيها صلاح إلا قضيتها يا أرحم الراحمين.

22. **“አላሁመ ላተደዕ ለና ዘንበን ኢላ ገፈርተሁ ወላዓይበን ኢላ ሰተርተሁ ወላሃመን ኢላ ፈረጅተሁ ወላደይነን ኢላ ቀደይተሁ ወላሃጀተን ሚን ሀዋኢጂ አዱንያ ወልአኺራ ሂየ ለከ ሪደን ወለና ፊሃ ሰላሁን ኢላ ቀደይተሃ ያአርሀመ ራሂሚን”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ወንጀላችንን ምንም ሳታስቀር ማርልን፤ ነውራችንን ሁሉ ሸፍንልን፤ ጭንቀታችንን በሙሉ ገላግለን፤ እዳችንን በሙሉ ክፈልልን፤ ከማንኛውም የዱንያም ይሁን የአኼራ ጉዳያችን ላይ አንተ የምትወደው ለኛም ጥቅም የሚያስገኝልንን ወስንልን፤ አንተ ከአዛኞች ሁሉ በላይ አዛኝ ነህና::

اللهم إني أسألك رحمة من عندك، تهدي بها قلبي، وتجمع بها أمري، وتلم بها شعثي، وتحفظ بها غائبي وترفع بها شاهدي، وتبيض بها وجهي، وتزكي بها عملي، وتلهمني بها رشدي، وترد بها الفتن عني، وتعصمني بها من كل سوء.

23. "አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ረህመተን ሚን ዒንዲከ ተህዲ ቢሃ ቀልቢ ወተጅመዓ ቢሃ አምሪ ወተሉመ ቢሃ ሸዐሲ ወተህፈዘ ቢሃ ጋኢቢ ወተርፈዓ ቢሃ ሻሂዲ ወቱበዩደ ቢሃ ወጅሂ ወቱዘኪ ቢሃ ዓመሊ ወቱልሂመኒ ቢሃ ሩሽዲ ወተሩደ ቢሃ አልፊተነ  ዓኒ ወተዕሲመኒ ቢሃ ሚን ኩሊ ሱእ"

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ልቤን የምትመራበትን፣ ጉዳዬን በሙሉ የምትፈጽምበትን፣ የተበታተነ ሃሳቤን የምትሰበስብበትን፣ ፊቴን የምታበራበትን፣ ስራዬን የምታጠራበትን፣ ትክክለኛ መንገዴን የማውቅበትን፣ ከኔ ላይ ፈተናህን የምትመልስበትንና ከክፉ ሁሉ እኔን የምትጠብቅበትን እዝነትህን እማጸንሃለሁ::

اللهم إني أسألك الفوز يوم القضاء، وعيش السعداء، ومنزل الشهداء، ومرافقة الأنبياء والنصر على الأعداء.

24. "አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አልፈውዘ የውመልቀዳእ ወዓይሸ አሱዓዳእ ወመንዚሊ አሹሃዳእ ወሙራፈቀተል አንቢያእ ወነስረ ዓለልአዕዳእ"

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! በፍርዱ ቀን መታደልን፣ የእድለኞችን ኑሮ፣ የሰማእታትን ስፍራ፣ ከነቢያት ጋር መጎዳኘትንና በጠላቶች ላይ የበላይነትን እለምንሃለሁ::

اللهم إني أسألك صحة في إيمان، وإيماناً في حسن خلق، ونجاحاً يتبعه فلاح، ورحمة منك، وعافية منك، ومغفرة منك، ورضواناً.

25. **"*አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሲሀተን ፊኢማኒን ወኢማነን ፊሁስኒ ኹሉቂን ወነጃሃን የትበዑሁ ፈላሀ ወረህመተን ሚንከ ወዓፊየተን ሚንከ ወመግፊረተን ወሪድዋነን*"**

**ትርጉሙ፦** *አላህ ሆይ! ጤንነትን ከኢማን ጋር፣ ኢማንን ከመልካም ስነ-ምግባር ጋር፣ ነፃ መውጣትን የሚያስከትል ውጤትን፣ ከአንተ ዘንድ የሆነ እዝነትን፣ ሰላምን፣ ምህረትንና ውዴታን እንድትለግሰኝ እለምንሃለሁ።*

اللهم إني أسألك الصحة والعافية، وحسن الخلق والرضى بالقدر. اللهم إني أعوذ بك من شر نفسي، ومن شر كل دابة أنت آخذ بناصيتها، إن ربي على صراط مستقيم.

26. **"*አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አሲሀተ ወልዒፊተ ወሁስነልኹሉቂ ወሪዳ ቢልቀደር አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ነፍሲ ወሚንሸሪ ኩሊ ዳበቲን አንተ አኺዙን ቢናሲየቲሃ ኢነረቢ አላ ሲራጢን ሙስተቂም*"**

**ትርጉሙ፦** *አላህ ሆይ! ጤንነትን፣ ጨዋነትን፣ መልካም ስነ-ምግባርንና ውሳኔህን መውደድን እንድትለግሰኝ እለምንሃለሁ። አላህ ሆይ! ከነፍሴ ክፋትና በአንተ ቁጥጥር ውስጥ ካሉ ተንቀሳቃሾች ሁሉ ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ። ጌታዬ ቃሉም፣ ስራውም፣ ፍርዱም ትክክለኛ ነው።*

اللهم إنك تسمع كلامي، وترى مكاني، وتعلم سري وعلانيتي، ولا يخفى عليك شيء من أمري وأنا البائس الفقير، والمستغيث المستجير، والوجل

المشفق المقر المعترف إليك بذنبه، أسألك مسألة المسكين، وأبتهل إليك ابتهال المذنب الذليل، وأدعوك دعاء الخائف الضرير، دعاء من خضعت لك رقبته، وذل لك جسمه، ورغم لك أنفه.

27. **“አላሁመ ኢነከ ተስመዑ ከላሚ ወተራ መካኒ ወተዕለሙ ሲሪ ወዓላኒየቲ ወላ የኽፋ ዓለይከ ሸይኡን ሚን አምሪ ወአነል ባኢሱል ፈቂር ወልሙስተጊሱል ሙስተጂር ወልወጂሉል ሙሽፊቁል ሙቂሩል ሙዕተሪፉ ኢለይከ ቢዘንቢህ አስአሉከ መስአለተል ሚስኪን ወአብተሂሉ ኢለይከ ኢብቲሃለል ሙዝኒቢ አዘሊል ወአድዑከ ዱዓአል ኻኢፊ አደሪር ዱዓአ መን ኸደዓት ለከ ረቀበቱሁ ወዘለ ለከ ጂስሙሁ ወረጊመ ለከ አንፉሁ”**

**ትርጉሙም፦** አላህ ሆይ! ንግግሬን ትሰማለህ ፣ ያለሁበትንም ትመለከታለህ፣ ሚስጥሬን እና ይፋ ያደረግኩትንም ታውቃለህ፤ ከጉዳዬ አንዳችም የሚሰወርብህ ነገር የለም። እኔ ችግረኛ፣ ድሃ፣ ዕርዳታህን፣ ጥገኝነትህን ፈላጊ፣ፈሪ እና የሚጨነቅ ወንጀለኛ መሆኑን የሚያምንና የሚያረጋግጥ ባሪያህ ነኝ። የደካማ ሚስኪንን ልመና እለምንሃለሁ። ወንጀሉ የከበደው ሰው መተናነስን እተናነስልሃለሁ፣ መዋረድን እዋረድልሃለሁ። መከራው የበዛበት፤ አንተን የፈራ ሰው መላ አካሉን ለአንተ ያስገዛ ያዋረደ ሰው ልመናን እለምንሃለሁ።፣ ሓጢአቱን የሚያረጋግጥና የሚያምን ሚስኪን አገልጋይህ ነኝ አላህ ሆይ! የሚስኪን ልመናን እለምንሃለሁ።

# በሱና መርከብ እንሳፈር

☞ በሱና ላይ ለመጠናከር አዳዲስና መጤ ከሆኑ አመለካከቶችና አምልኮዎች እራስን ማላቀቅ ያስፈልጋል፡፡ በዲን ዉስጥ አዲስ መጤ ነገር ሁሉ ቢድዓ ነዉ፡፡ ቢድዓ ደግሞ የተወገዘ ነዉ፡፡ መልዕክተኛዉ እንዲህ ብለዋል **‹‹በዚህ በጉዳያችን (በዲናችን) ከእርሱ ያልሆነን ነገር የፈጠረ (ስራው) ተመላሽ ነው፡፡››** ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ በሌላ ተመሳሳይ ሀዲስ ፡- **‹‹ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ (ስራው) ተመላሽ ነው፡፡››** ሙስሊም ከዓኢሻ ዘግበውታል፡፡

☞ ኢስላም የተሟላ በመሆኑ ምንም አይነት ጭማሪን አይቀበልም፡፡የተላለፈልንን ሱና ብቻ ብንተገብር ተጠቃሚዎች እንሆናለን፡፡ ታላቁ ሰሀቢይ ኢብን መስዑድ እንዲህ ብለዋል፡- **"ተከተሉ! ቢድዓንም አትፍጠሩ! ሱና በቂያችሁ ነውና!!" ፡፡** ሁዘይፋ ኢብኑል የማን ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡- **‹‹የመልዕክተኛው ሰሃቦች**

ባልሰሩት ማንኛውም የዒባዳ ተግባር አምልኮን አትፈፅሙ! የመጀመሪያዎቹ ለመጨረሻዎቹ ምንም የተዉት ነገር የለም!›› አቡ ዳዉድና ሌሎች ዘግበውታል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ‹ምንም እንኳ ቢድዓ ቢሆን ጥሩ ስለሆነ ቢድአቱል ሀሰናህ ነዉ› ይላሉ፡፡ ለዚህ ምላሹ ተከታዩ የዓብዱላህ ኢብን ዑመር ንግግር ነዉ፡፡ ‹‹ሁሉም የቢድዓ ተግባር ጥመት ነው! ሰዎች መልካም አድርገው ቢያየዩት እንኳ!›› ኢብኑበጣህና አል-ላላካኢይና ሌሎችም በትክክለኛ ሰነድ ዘግበውታል፡፡

አል-ኢማሙ ማሊክ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹አንድ ሰዉ፤ በኢስላም ውስጥ አዲስ ነገርን ፈጥሮ ያ ፈጠራ ጥሩ መስሎ ከታየው ነቢዩ መልእክታቸውን አጓድለዋል ብሎ ጠርጥሯል፤ ያኔ ዲን □ልነበረ ዛሬ ዲን አይሆንም!›› ፡፡

ሙስሊም ወንድሞችና እህቶች! ለብዙ ሰዎች ሱናን ተግብሮ ሱኒይ መሆንን ከባድ የሚያደርገዉ ለመጤ

አመለካከቶችና ተግባሮች ልባቸዉን መስጠታቸዉ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ሙስሊም አላህን በመፍራት ሀቅን ሊከተል ይገባዋል፡፡ አቡበከር ኢብኑል-ዓያሽ **‹ሱኒይ ማን ነዉ?›** ተብለዉ ሲጠየቁ **‹የፈጠራ መንገዶች ሲጠቀሱለት ምንም ወገንተኝነት የማያሳይ ነዉ›** ኪታብ አሽሪዓ ሊልአጁሪይ ቁጥር 2058

☞ **አል- ኢማም ማሊክ ኢብኑ አነስ እንዲህ** ብለዋል፡- **‹‹ሱና የኑህ መርከብ ናት! የተሳፈረባት ይድናል! ወደኋላ የቀረ ይሰጥማል!››** ሚፍታሁልጀናህ 46

**ሱናን አዉቀን በመተግበር ሁላችንም በኑህ መርከብ እንሳፈር!!!**

# ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

በሰኔ ወር 2001 ዓ.ል ተመስርቶ በተቀናጀ መልኩ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።

## የማዕከሉ ዋና ዋና ክፍሎች

- የዓረብኛ ቋንቋና የሸሪዓዊ ጥናቶች ኢንስቲትዩት(ለወንዶችና ለሴቶች)
- የቁርዓን ሒፍዝ ክፍል - ለሴቶችና ለወንዶች
- የቤተ መፃህፍት አገልግሎት
- የህፃናት የኢስላማዊ ትምህርትና የተርቢያ ማዕከላት
- የመድረሳዎችና የዱዓቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ መስጫ እና የካሪኩለም ማሻሻያ
- የኢንተርኔት ዳዕዋ ማዕከል
- የድምፅ ቅጂ ስቱዲዮ
- መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ ትምህርት መስጫ
- ሙስሊም ላልሆኑና በቅርቡ ለሰለሙ የዳዕዋና የትምህርት አገልግሎት መስጫ
- ለዲን ተማሪዎች መደበኛ ያልሆነ የአካዳሚ ትምህርት
- የተለያዩ ኪታቦች የሚቀሩበት የሐለቃ ቂራዓት ለወንዶችና ለሴቶች

**የማዕከሉ አድራሻ:-** ☎ +251112781893

www.nesiha.org

e-mail:-info@nesiha.org

Fax: +251112779660

# مركز ابن مسعود الإ سلامي

أُنشِئ مركز ابن مسعود الإسلامي في شهر شعبان سنة **1430** هـــــ، وقد حصّل المركزعلى شهادة الرّخصة من وزارة العدل الإثيوبي برقم **0034** ليمارس أنشطته كهيئة دينية رسميّة.

## أقسام المركز

- يشمل المركز عدّة أقسام منها :-
- معهد اللغة العربية والدراسات الإسلاميّة (للبنين وللبنات)
- مركز تحفيظ القرآن الكريم (للبنين وللبنات)
- مراكز لتعليم القرآن الكريم وتربية الأطفال
- قسم كفالة الدعاة والمدرسين ودعم المدارس وتطوير المناهج الدراسية
- المكتبة العلميّة
- مركز الدّعوة عبر الإنترنت
- استوديو لتسجيل المحاضرات

- قسم تعليم الصم بلغة الإشارة
- مركز الهِداية لتعليم المهتدين الجدد
- محو الأمّيّة عن طلبة العلم الشرعي
- قسم الدّروس والحلقات العلميّة

## عنوان المركز:

☎ +251112781893
www.nesiha.org
e-mail: info@nesiha.org
Fax: +251112779660




# دليل الحاج والمعتمر وزائر مسجد الرسول ﷺ

إعداد: هيئة التوعية الإسلامية في الحج

ترجمة: طه أحمد

مركز ابن مسعود الإسلامي
أديس أبابا – إثيوبيا
طبع على نفقة بعض المحسنين




**Ibnu Maso'ud Islamic Center**

e-mail: info@nesiha.org
www.nesiha.org
Telphone: +251-112-781893
Mobile Phone Number: +251-911-515102
Fax: +251112779660
P.O.Box: 50151
Location: Lideta Street Abnnet Area near Jos Hanson
Addis Ababa
Ethiopia